# ጂኒየስ መሆን እንዴት ይቻላል!

በመረጥከው የትምህርትና የሙያ ዘርፍ ጂኒየስ ለመሆን የሚያስችልህ የተሟላ መመሪያ



2010 ዓ.ም

# ጂኒየስ መሆን እንዴት ይቻላል!

ባ/ኪ/ቱ/ጽ/ቤት
መ.ቁ 15፰
Sub City Woreda 10 Administration
Culture Arts & Tourism Office

2010 ዓ.ም

የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

All Rights Reserved

© ሚሊዮን አስማማው

ያለ አዘጋጁ ፈቃድ መጽሐፉን ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ማባዛት፣ ማተምና ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው።

2010 ዓ.ም

የዚህ መፅሀፍ መታሰቢያነት ሳትማር ትምህርትን እና መማርን እንዲሁም ጠንክሮ መስራትን ታበረታታ ለነበረችው ዛሬ በህይወት ለሌለችው ለውድ እናቴ ለወ/ሮ ሙሉፀሐይ እንተነህ እያሌው ነው፡፡

# ምስጋና

ይህን መፅሀፍ ሳዘጋጅ ለረዱኝና ላገዙኝ በብዙ መልኩ ለታገሱኝ ለመላው ቤተሰቦቼና ለወዳጆቼ በተለይም ለአቶ ግርማ በሻህ እና ለሄኖክ ብርሃኑ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

ክፍል አንድ ........ 1

በውስጣችን ያለው ምጡቅነት ........ 1

የብልሃት ልኬት ........ 3

የብሩህነት ጠቋሚዎች ........ 3

እንደምጡቅ ማሰብ እንዴት እንደሚጀመር ........ 7

እርከን 1፡ አንግር ........ 7

እርከን 2፡ መፍትሔዎችን በአእምሮህ ተመልከት ........ 7

እርከን 3፡ ሥራ አትፍታ ........ 8

እርከን 4፡ ያልተለመደውን ልመድ ........ 8

እርከን 5፡ ተቃራኒውን ፈልግ ........ 8

እርከን 6፡ አመሳስል ........ 9

እርከን 7፡ ደግመህ ደጋግመህ ሞክር ........ 9

ክፍል ሁለት ........ 10

ዞን ውስጥ መግባት ........ 10

ንቁ አእምሮ እና ስውር አእምሮ ........ 10

ዞን፣ ምንነቱና እንዴት እንደሚደረስበት ........ 11

ዞን፣ ክህሎት፣ቁርጠኝነት እና ፍላጎት ........ 13

ማናቸውንም ክህሎት ይዞ "ዞን" ውስጥ መግባት ........ 16

በዞን ውስጥ መግባት፣ ጊደም ........ 18

እርከን 1፡ ተግዳሮት ይኑርህ ........ 18

እርከን 2፡ ግብህን ተመልከት ........ 18

እርከን 3፡ ሙሉ ትኩረትህን ስጥ ........ 18

የተውሶ ልሂቅ ብልህነት ፤ የጭንቅላት ልውውጥ ጥበብ ..... 45
የተውሶ ጂኒዩስን ነፃ ስለመልቀቅ ..... 47
ስለጭንቅላት ልውውጥ ከፍተኛ ቴክኒክ፣ ዝግጅት ..... 49
ባለ አስር ደረጃ የስኬት ጉዳና ..... 49
የተሟላ የላቀ የጭንቅላት ልውውጥ ቴክኒክ ..... 50
የጥያቄና መልስ ፤ ወዲያው ! ..... 52
ክፍል አምስት ..... 53
የቃላት አስማታዊ ኃይል ..... 53
ክፍል ስድስት ..... 57
ቁጥሮችን በፍጥነት ማስላት ..... 57
ቁጥሮችን መጠቀም፣ መሠረታዊ አሠራሮች ..... 58
ካልኩሌተር ጣት ..... 60
የማባዛት አስማት ..... 61
የሂሳብ ፕሮብሌሞችን በፍጥነት ለመፍታት 10'ን መፈለግ ..... 63
11 የሚመች ቁጥር ነው ..... 65
ቀለል ያለ መቀነስ ..... 67
በመደመር የመቀነስ ውጤትን ማረጋገጥ ..... 68
"ክፋፍለህ ግዛ !" (Division) ..... 69
ወደ ሜትሪክ መቀየር ..... 71
ኩባያዎች እና ጆጎች ..... 72
ክፍል ሰባት ..... 73
የማስታወስ ችሎታ ተአምር ..... 73
ቁጥሮች እና ምህፃረ ቁጥሮች ..... 74

ክፍል አስር ........ 112

የማግባባት ጥበብ ........ 112

- ተደማጭ መሆን ........ 113
- ሰዎች ለምንድን ነው በተለመደ ዘይቤ የሚንቀሳቀሱት ........ 113
- የድግግሞሽ ጠቃሚነት ........ 114
- ትክክለኛዋን ቁልፍ ለመጫን ትክክለኛ ጥያቄ አቅርብ ........ 114
- ሚረሪንግ ግንኙነት ይፈጥራል ........ 115
- አተነፋፈስ፤ ድምጽ፤ እጅ አወራወር፡ ........ 116
- "የማግባባት ቀመር" እና አተገባበሩ ........ 117
- ቃላትን በሀይል እና በስሜት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ........ 118

ክፍል አስራ አንድ ........ 119

መሠረታዊ የፍጥነት ንባብ መግቢያ ........ 119

- ልታሸንፋቸው የሚገቡ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፦ ........ 119
- 1. የፍጥነት ንባብና አንጎልህ ........ 120
- 1. እንዴት እንደምታነብ ........ 123

ክፍል አስራ ሁለት ........ 172

የፈጣን ንባብ ችሎታን የበለጠ ማሳደግ ........ 172

- የፈጣን ንባብ ጥበብ፣ የእጅና የአይን ቅርክና ........ 175
- 2ኛ ክፍል ንባቡን ማፍጠን ........ 177
- እያንዳንዱን ገጽ በፍጥነት ማንበብ ........ 180

ክፍል አስራ ሶስት ........ 181

ብልህነትን በይብልጥ ማሳደግ ........ 181

- ማስታወሻ መያዝ ........ 182

ፎቶ ንባብ፦ በአንጎል ማንበብ (ላቅ ያለው የንባብ ክህሎት)......184
የፎቶ ሪዲንግ ቅድመ ዝግጅት......186
ፎቶ ንባብ......186
ክትትል......187
ነፃ ማስታወሻ፡ ሀሳብን በተከሰተበት ጊዜ መጻፍ......188
የነፃ ማስታወሻ አያያዝ......189
የአእምሮ ካርታ ማስታወሻ......190
"ብሬይንስቶርሚንግ"......192
የግል ፕሮብሌም አፈታት......194
የአእምሮ ካርታ ማስታወሻን መፈተሽ......195
መደምደሚያ......197

ይህ መጽሃፍ ትምህርትን ፣፣አያጣጥልም፣፣፤ እንዲያውም ሀቁ ተገላቢጦሹ ነው። በትምህርት የገፋ ሰው አንዳንድ ፅንሰሃሳቦችን ለመገንዘብና የቴክኒክ መረጃዎችን ለመጨበጥ ቀላል ይሆንለታል። በየትኛውም የእውቀት ደረጃ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሰው በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን ዘዴዎችና መመሪያዎች በማንበብ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ይህን መጽሐፍ ስታነብ መልመጃዎቹን በኋላ እመለስባቸዋለሁ ብለህ ዘለህ ወደፊት የመሄድ ፍላጎት እንዳይፈታተንህ። "እንጎል ማስፊያ ዘዴ" ተብለው የተቀመጡትን መልመጃዎች በመጀመሪያው ዙር ከተጋተርካቸው የእያንዳንዱ የመልመጃ ዘዴ የፈጠራ ክህሎትን ለመቀስቀስና የኋላኋላ ለማሳደግ ያለህን እምቅ ኃይል እየተዋወቅከው ትሄዳለህ ማለት ነው። በመጨረሻም፤ ሊዘነጋ የማይገባው አንድ ነገር ቢኖር እንድን መልመጃ ደጋግመህ በሞከርከው ቁጥር ክህሎቱን በበለጠ እንደምትላመደውና፤ ለወደፊቱም የበለጠ እንደሚቀልህ ሀቅ መሆኑ ነው።

ይታወቃል። ሌሎችን መሰፈርቶች በተመለከተ እሚልቶ መገኘቴንና አለመገኘቱን የሚያውቁት የቅርብ ወዳጆቹ ብቻ ናቸው።

ነገር ግን እንደምጡቅ ለማሰብ ትችል ዘንድ ሁሉን ለማወቅ መንጠራራት አያስፈልግህም። በዚህ መፅሀፍ የተሰጠው ትንተና መዳበር ያለባቸውን ችሎታ እንድታዳብር፣ ክህሎትህን ከፍ እንድታደርግና በመጨረሻም ሌሎች ችሎታዎችህ አንፀባርቀው እንዲወጡ መርዳት ነው።

## እንደምጡቅ ማሰብ እንዴት እንደሚጀመር

እንደባለሙያ ለመስራት የግድ ባለሙያ መሆን የለብህም የሚል ጥንታዊ ብሂል አለ። ብሂሉ ጂኒየስንም ይመለከተዋል ። እንዴ እነኚያ ልሂቆች የተጠቀሙበትን ጥበብና ስትራቴጂ በሚገባ ስታውቅና የነሱን ፈለግ ተከትለህ ከሄድክ የራስህን የፈጠራ ችሎታ በተግባር ልትተረጉመው ትችላለህ። ስለዚህ ምንም እንኳ ጂኒየስ አለመሆንህን ብታምንበትም፣ እንደጂኒየስ የማሰቡን ዘዴ ግን ልትማረው ትችላለህ።

### እርከን 1፤ አንፃር

አንድ ምጡቅ ችግርን ከብዙ አንፃር ነው የሚመለከተው፣ ከራሱ ወይም ከራሷ አንፃር፣ ከሌላው ሰው አንፃር፣ ከተቃራኒ አመለካከት አንፃር ወዘተ፤ ብሩህ አእምሮ ያላቸው ሰዎች ሁሉ ሌላው መለያ ባህሪያቸው፤ ምንም ነገር በቀላሉ አለመቀበልና ያልተፈታ ችግር በመረጠበት ጊዜና ቦታ ወቅቱን ጠብቆ ሲመጣ ማስተናገድ ነው።

### እርከን 2፤ መፍትሔዎችን በአእምሮህ ተመልከት

የራስህን ችግር በራስህ ለመፍታት በቃላትና በፅሑፍ ላይ ብቻ እምነትህን አትጣል። ችግሩን በስዕል ወይም በዲያግራም መልክ ለማየት ሞክር፤አይንስታይን እንዳደረገው ስዕሉን አቅልመው፤ ቅርፅ ስጠው ባለሶስት ልኬት አድርገው። ሌሎች ዘዴዎች ሁሉ ተሞክረው መልሱም ጥቂት የቀረው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ነው በቃላትና በፅሑፍ ልትጠቀም የምትችለው።

## በዞኑ ውስጥ መግባት፣ ጊዜም

በዞኑ ውስጥ ከመግባት ጋር አብሮ የሚመጣውን ትኩረትና ግልፅነት ለማግኘት ማድረግ የሚገባህ ሂደቱን ወደ ጊዜም መቀየር ነው። እንደማናቸውም ጊዜም ይህም የሚከበር የራሱ የሆነ ደንብና የአካሄድ ስርዓት አለው። እዚህ ላይ ሊበነጋ የማይገባና አንድ ነገር ቢኖር፣ ከሁሉ በፊት ጊዜሞችን እጅግ ተወዳጅ የሚያደርጋቸው ደንባቸውና እጨዋወታቸው መሆኑ ነው።

### እርከን 1፣ ተግዳሮት ይኑርህ

ሽንቅጥ ለማለት ትፈልጋልህ እንበል ። የስፖርት ትጥቅ ትገዛና ለመጀመሪያ ጊዜ የ15 ደቂቃ ሶምሶማ ለመጀመር ቆርጠህ ትነሳለህ። ደንቡ የሚለው ስልከም ሆነ ሰው ሳያቋርጥህ የ15 ደቂቃ ሶምሶማ ፈጽም ነው።

ስንት ደቂቃ እንደሮጥክ ለማወቅ ሰዓትህን መመልከት ነው።

### እርከን 2፣ ግብህን ተመልከት

ደንብ አውጥተህ የሶምሶማውን መርሃ ግብር ጀምረሃል። መርሃግብሩን ጀምረህ ሶምሶማውን እያካሄድክ እያለ አእምሮህ በጥቂቱም ቢሆን ሊያፈነግጥ ይችላል። በዚህ ጊዜ አሳማህ እንዳይሸረሽርና መሻሻልህን በቅርብ ርቀት ለመቆጣጠር እንዲያስችልህ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ የሶምሶማ ሂደቱን መቆጣጠሪያ 15 ደቂቃ መሆኑ ቀርቶ በየአምስት ደቂቃው ልዩነት እንዲያሳስብህ ቀይረውና ጮክ ብለህ "ሸንቃጣ መሆን እፈልጋለሁ!" ስትል ራስህን አሳስበው።

### እርከን 3፣ ሙሉ ትኩረትህን ስጥ

ሙሉ ትኩረትህ በጊይሙ ላይ መሆን ይኖርበታል። አንድ በአንድ የምትወስዳቸው እርምጃዎች ሁሉ፣ በረጅሙ ግብህ ለምታስመዘግበው የድል ምዕራፍ ሊያዘናጉህ የሚሹትን ሀሳቦች ሁሉ ሊያጠፏቸው ይገባል።

### እርከን 4፤ ጌይሙን በጌምነቱ ውደደው

ጌይሙ ራሱ አስደሳችነቱን ያስመስክር፡፡ አንድ ግብ ለመምታት ራስህን ማስገደድ ሳያስፈልግህ ግቡን ለመምታት የሚደረገውን ሂደት አጣጥመው፡፡

### እርከን 5፤"የገባኝ" ወቅት

በመጨረሻም ጌይሙ ምቹና ተስማሚ በሚሆንበት የተፈጥሮ ደረጃ ላይ ትደርሳለህ ፡፡ ይህ ነጥብ በአናሳ ጥረት ብቻ ወደ ዞኑ የምትገባበትና ያለምንም ድካም ትኩረት ማድረግ የምትችልበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሳታስበው በሚደርስ ሁኔታ፣ ተመስጦ ውስጥ መግባትህ ይሰማሃል፡፡

### እርከን 6፤ ከፍታ መድረስ

ዞኑ ውስጥ መግባትህ እውን መሆኑን ተከትሎ የተደነቀብህን ተግዳሮት የማሸነፍና አልፎም የመዝለቅ አዲስ ሃይልና የቁርጠኝነት መንፈስ ይጠናወትሃል፡፡ ጌይሙን በተጫወትህ ቁጥር ተግዳሮቶችህን የማሸነፍህ እድል እየሠፋ ከዚያም አልፈህ ለመሄድ አዲስ ተግዳሮቶችን ለመጋተር ይረዳሃል፡፡

ይህ " ዞኑ ውስጥ የመግባት" ጌም ለምትወጥነው ተግባር ወይም ለምታስቀምጠው ግብ ሁሉ በአጋዥነቱ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ የውጭ ቋንቋ ለመማርም ሆነ የከርስ ባህር (አንደር ወተር) ፎቶ ግራፍ ለማንሳት፤ ሂደቱ አንድና አንድ ነው፡፡ ሀሳብህ ከጌይሙ ማስቀፍ ውጭ እስካልሆነ ድረስና የጌሙን ህግ እስከተከተልክ ድረስ በየቀኑ የምታገኘው ውጤት ተመሳሳይ ነው፡፡

የ15 ደቂቃ ልምምድ ካደረግህ በኋላ "ወደ ዞኑ የምትገባ ትሆናለህ" ብሎ ለመገመት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሙከራዎች ወቅት ለውጥ መጠበቁ ምናልባት የማያዋጣ ሊሆን ይችላል፡፡ ሂደቱን እየተላመድክ እንዲሁም [illegible] እያጋጠሙ አዲስ ሙከራ ከዚያ በፊት ከተሞከሩት በበለጠ ወደ ዞኑ እንዲደርስህ ይመጣል፡፡

ይህ ነው ትክክሉ ዘዴ ለማለት ስለማይቻል የሚያመችንን መንገድ ይዞ መዝለት ነው የሚያዋጣው፡፡

ስለዚህ አምስት የምልከታ መንገዶችን እንዘርዝር ፡፡ እንደ ምርጫችን እያንዳንዱ ዘዴ የሚያስኬድ ነው፡፡ ማድረግ የሚገባን የሚስማማንን ዘዴ መምረጥ ነው፡፡ እንዲያውም የፈለገ ሁሉንም ፈትሾ ሁሉንም በአንዴ ሊጠቀምባቸው ይችላል፣ ምርጫው የሱ ነውና፡፡

## አምስት የአእምሮ ምልከታ ዘዴዎች

አምስቱ የምልከታ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ማዋሃድ፡- ምስሎችን በአእምሮ አይን መመልከት፤
2. መፈንጠቅ፡- ክስተቶችን መፈንጠቅ ወይም ማሰራጨት፤
3. ትንበያ፣ በምናብ ባየነው ኩነት ውስጥ ራሳችንን ተዋናይ አድርገን መመልከት
4. ስሜታዊ ማድረግ፡- ምንም ነገር በዓይናችን ሳንመለከት ስሜት እና የስሜት ኃይልን መዳሰስ፤
5. ወግ፣ስለአንድ ጉዳይ፣ ኩነት፣ድርጊት ማውጋት

እነዚህ አምስቱን ብልሃቶች አንድ በአንድ ከመቃኘታችን በፊት የአእምሮ ምልከታ የተሰኘውን ጽንሰ ሀሳብ አጠቃላይ ዳሰሳ እናካሂድ፡፡ ቁም ነገሩ ምልከታ የሚለውን ቃል ሙጥኝ ብለን አዳንቀር ወይም ምናባዊ ስዕሎች በመመልከት እንዳንታቀብ፡፡ ነገሮችን በቀላሉ ተመልከታቸው፡፡

ለምሳሌ ምልከታህን ሁልጊዜ በምትመኘው አዲስ መኪና ላይ አሳርፈው ወይም በሃሳብህ የኖርክበት በባህር ዳርቻ ያለውን ቤትህን ተመልከት፡፡ ስለዚህ ትዝታዎች ስታስብ ስለነሱ ምናልባት አንድ ስዕል ይታይሃል ወይም ትዝታ ይሰማሃል፡፡ የአእምሮ ምልከታ የምንለው ይህንኑ ነው፡፡

ወይም የተናደድክበትን፣ የፈራህበትን ጊዜ ልታስታውሰው ትችላለህ፡፡ የደረሱብንን ሁኔታዎች በምሬት (በጠንካራ ስሜት) ማስታወስ አንድን ቦታ እና ድርጊትን በቀላሉ ያስታውሰናል በተለይ መጥፎ ነገር ሊደርስብን ይችላል ብለን የምንጠብቅ ከሆነ፡፡

* ሙከ ብለህ ስለ አንድ የታወቀ ቦታ ፤ ስለአንድ የቤተሰብ አባልህ ወይም ወዳጅህ ገላጭ ሃተታ ስጥ ፤
* የምትጠቀምበት ግሥ ያሁኑን እንጂ ያለፈውን ጊዜ መግለጥ አይኖርበትም ፤ ለምሣሌ ፡- የአይፍል ታወር በብረት የተሠራ ‹‹ሌ›› ይመስላል ። ‹‹ብሌን ጠይም ፊቷም ክብ ነው ››።
* በህዋሳትህ የምታገኘውን መረጃዎች ፤(ማለትም በእይታ ፤ በማዳመጥ ፤ በማሽተት ፤በመዳሰስ በማጣጣም ፤ በቆዳ ስሜት) በተቻለ መጠን ዘርዝር አድርገህ አቅርባቸው ።

ስለ ሥዕለ አእምሮህ (ሜንታል ኢሜጅ) ገላጭ ሃተታ ሙከ ብሎ መስጠት ማስፈለጉ የአእምሮ አይታህን ተጨማሪ ኃይል ስለሚሰጠው ነው። በተጨማሪም ፤ ለአንጎልህ ቅጽበታዊ ግብረመልስ ይሰጣል ፤ ይህም የአእምሮ አይታህ ሥራውን እንዲቀጥል ይረዳዋል። ገላጭ ሃተታህን በአሁን ጊዜ ግሥ (ፕሬዜንት ቴንስ) ማድረግህ በራስህ የአእምሮ ኃይል የፈጠርከውን ሥዕለ አእምሮ አሁኑኑ እዚሁ በመፈጸም ላይ ያለ ድርጊት ያስመስለዋል።

እነዚህ ቴክኒኮች የአእምሮ ምልከታን መሠረታዊ ክሂሎት ያስጨብጡሃል። ሞክረህ ካልሠራልህ ፤ አትጨነቅ ። ሁነኛ ዘዴ ከተሰጠውና ሁኔታዎች ከተመቻቹለት የማንም አእምሮ ‹‹ሊያይ›› ይችላል ። የአእምሮ ምልከታህ ሥራውን ይቀጥል ዘንድ የሚያግዙ ተጨማሪ መመርያዎች እነሆ፤-

## የትዝታ ትእይንት

በተፈጥሮ ውበቱም ሆነ በሌላ ምክንያት ልዩ ትዝታን የጣለብህን ከዚህ በፊት የጐበኘኸው የምትወደው ቦታ ትዝ ይበልህ ። በተቻለህ መጠን በዝርዝር ሁኔታዎችና በህዋሳዊ መረጃዎች በታጀበ መልኩ ስለዚያ ቦታ ከፍ ባለ ድምፅና የአሁን ጊዜ ግስ በመጠቀም ገላጭ ሃተታ ስጥ። ሥዕሎች ከመጀመርያው ትርዒታቸው ወጣ ያሉ ቢሆኑም ዝም ብለህ የሚታይህን ከመግለፅ ወደ ኋላ አትበል።

በዝርዝር ሁኔታዎችና በህዋሳዊ መረጃዎች የታጀበ መሆን ይኖርበታል። ይህ ሲሆን ብቻ ነው ትእይንቱን ሕይወት ልታላብሰው የምትችለው ።

## የአእምሮ እይታን ማሻሻያ አራት ደረጃዎች

የአእምሮ እይታህ ከህሉት እየተሻሻለ በመጣ ቁጥር ፤ በአእምሮ የሚቀረፀው ሥዕልም በዓይነት እና በደረጃም ይገዝፋል ። የአእምሮ እይታ የፈጠራ ሂደት መሆኑን አትዘንጋ ፤ የእይታውን ሥራ ያለመስለስ ከተያያዝከው ፤ የተቀመረ ጥረት ሳያስፈልግ ሥዕሎች በአእምሮህ ውስጥ ድቅን እንደሚሉብህ እሙን ነው ። ይህም፤ ከዚህ በፊት እንዳየነው ሁሉ የአእምሮ እይታ ጡንቻን ለማፈርጠም የተደረገ ጥረት ውጤት ነው።

በአእምሮ እይታህ የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን ጉዳዩን እንዳቅሙ በተደራጀ መልኩ መመልከት አስፈላጊ ይሆናል ፤ ለዚህም በተቀናጀ ዘዴ በመጠቀም እይታውን ለመቆጣጠር ብሎም አንተ ራስህ ያየኸውንና የሚሰማህን በውል ክትትል እንድታደርግ ለማብቃት ነው ። ይህን በተግባር ለመተርጎም የሚያስችሉህ አንዳንድ መመሪዎች ከዚህ በታች አስቀምጠናል።

### እውን እንደሆነ አቆየው

የአእምሮ እይታን ገላጭ ሃታታ በአሁን ጊዜ ግስ ማተቱ ማለትም ‹‹የአሁኑና የዚሁ ድርጊት›› ሆኖ እንዲቀጥል ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ አቅም በፈቀደ መጠን ሕዋሳዊ መረጃን በብዛት ማካተት ጥሩ ሀሳብ ነው። በምናብ እይታ የሚከሰተውን ምስል ብንለውም ብዙ ሰዎች በምስል እይታ ብቻ አይተማመኑም ። በሌሎችም አእማደህዋሳት ለመጠቀም በመሻት ለሚሰሚቸው ድምጾች፤ ለሚያሸቷቸው ሽታዎች፤ቆዳቸው የዳሰሰውን ስሜት፤በዳበሳ የተገኘውን ልስላሴ ወይም ሻካራነት ምላስ ያጣራውን ጣዕም ወዘተ በግምገማ መሣርያነት ለመጠቀም ይሻሉ። ልብ የምትለው እያንዳንዱ ተጨማሪ መረጃ የአእምሮ እይታን እውነተኛነት እና አግባብነት ያለው ያደርጋዋል።

**ተያያዥነት**

አእምሮ ላይ የሚቀረፅ አንድ ሥዕል በአብዛኛው ጊዜ ስለሌላ ኩነት እንድታስብ ያደርግሃል፤ ያ ኩነት ደግሞ የምታውቀውን አብረሃቸው የኖርክ ሰዎችን ማግኘት ሊሆን ይችላል። እነዚህ ተያያዥ ትዝታዎች በአእምሮ ውስጥ ተሸክፈው የኖሩ ምስሎችን ፈትቶ ከመልቀቅ አልፈው የፈጠራ ኃይልህን ዳርድንበር ያሰፋሉ።

**ማስታወሻ መያዝ**

የምናብ እይታን ነፀብራቅ በየዕለቱ የሚመዘግቡ ሰዎች አሉ። በምናብ የምታያቸውን ሁሉ በማስታወሻ ይዞ ክትትል በማድረግ ፤ በመጨረሻም የአእምሮ እይታህን መኖርያቸው ላደረጉ ሥዕሎች ከፍተኛ ግምት እና እውቅና እስከመስጠት ትደርሳለህ። እያንዳንዱ ግለሰብ ነገሮችን የሚያየው ከራሱ አንፃር መሆኑን ፤ያንተም እይታ ለአንተ ብቻ አግባብነት ያለው ብቸኛ እይታ መሆኑን አስተውል።

**በድምዳሜ ላይ ማተኮር**

የአእምሮ እይታ የሚለዉ ፅንሰ ሃሳብ በቀኝ አንጎላችን መጠቀምንም ያጠቃልላል ። ይህም አስተሳሰብህ እንዲቦርቅና በተፈጥሮ የታደልከውን የመፍጠር ችሎታ ሙሉ አርነቱን እንዲጎናፀፍ ያደርገዋል። አእምሮህ በብዛት እይታ እያደረገ በሄደ ቁጥር ስውር አእምሮ ለፈጠራ ፍሰት የበለጠ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ የአእምሮ እይታህ የመጨረሻው ክፍል ከበፊቱ ከነበሩት ሁሉ በበለጠ ፈጠራ የሞላበት ከመጀመሪያው የበለጠም ደፋር ይሆናል። ስለዚህ ፤ምስሎቹን በምትፈትሽበት ወቅት ልትዘነጋው የማይገባ ፤ በአእምሮ እይታው ማብቂያ ገደማ የተቀረፁትን ምስሎች በዓይነ ቁራኛ እንድትይዛቸው፤ እነዚህ ምስሎች ከፍተኛ የሆነ ንፁህ የፈጠራ ኃይል የፈሰሰባቸውና ታላቅ ግምትም ሊሰጣቸው የሚገባቸው ናቸውና።

## የቀን ህልም ጠቀሜታ

በጥናት እንደተረጋገጠው "የቀን ህልም" (ዴይድሪሚንግ) ለአእምሮህ እምቅ የሆነ የፈጠራ ችሎታና የላቀ ብልሃተኛነትን ይሰጠዋል። ይህ ደግሞ የማይካድ ሐቅ የሚያደርገው ሁለቱ የአንጎላችን ክፍሎች በትብብር እንዴት እንደሚሰሩ ስንገነዘብ ነው።

በአስቸኳይ የሚፈለግ ይህ መልስ ምናልባትም ወጭ ሆኖ ድንገት ብልጭ ሊልህ ይችላል ፣ ነገር ግን በወትቱ በንቁ አእምሮህ በመጠቀም በሥራ ተጠምደህ ስለነበር ልብ ሳትለው ቀርተህ ይሆናል ። ለዚህም ይመስላል ቀን ህልም ውስጥ ገብተህ የሚቀርቡልህን መረጃዎች ያለሂሳዊነት ለመቀበል ዝግጁ ሆነ ሳለ መልሶቹ ብቅ የሚሉት።

አያሌ ሰዎች በቀን ህልም ዓለም ውስጥ ገብቶ ነገሮችን ማውጣት ማውረዱን መርሃ ግብር ይዘውለት በመደበኛነት በየዕለቱ የሚያዘወትሩት ተግባር አድርገውታል ። ትኩረታችን በአንድ ጉዳይ ላይ አተኩሮ ሊቆይ የሚችልበት የጊዜ መስፈርት ከ90ደቂቃ እንደማይበልጥ በሰፊው የታወቀ ሐቅ ነው ። እነዚህን ሁለት ነጥቦች በግምት ውስጥ በማስገባት ፣ አንድ ሁለቱ ጠዋት፤ አንድ ሁለቱ ከሰዓት እና ወደማታም እንደምናልም በተወሰነ እርግጠኝነት ለመተንበይ ይቻላል። የጉብኝት መርሃግብሩ በየእለቱ ስንቴ እንደሚፈጸምና እንደሚመጣ እናውቃለን ፤ ቁም ነገሩ በሚከሰትበት ጊዜ ዝግጁ ሆኖ በመገኘቱ ላይ ነው ።

በእርግጥ ይህ ‹‹የቀን ህልም›› የሚከሰትበት ወቅት በናፍቆት የሚጠበቅ የፈጠራና የመነሳሳት ምንጭ ነው፤ ነገር ግን በየእለት ኑሯችን ‹‹እነሳሽ እማካዮች›› ለመፍጠር የሚያስችሉን ነገሮች እንዳሉ መዘንጋት የለብንም ።

<u>ምልከት ጠብቅ</u>

የጀንበር ጥልቀት፣ ርጭ ያለ ሐይቅ ፣ጥርት ያለ ሰማይ፣ የህፃን ፊት ፣ ልዩ ትርጉም ያለው ዘፈን በምናብህ ይታዩሃል እንበል። ከዚች ዓለም የዕለት ተለት ውጣውረድ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ሕዋሳችንን ገለል ማድረጉ አዲስ አስተሳሰብ ለመፍጠር ይገፋፋል።

ሁሉንም ለማሟላት ባይሳካልህም ፤ ገጠመኞችህን የምትከትብበት ወረቀትና ስክሪፕቶ እንዳይለይህ ። ቀጥሎ ያለው ምዕራፍ እንደሚያስረዳው " ዱድሊንግ " (መሞነጫጨር) ታሥሮ የነበረውን የፈጠራ ችሎታችንን ባልተለመደ መንገድ ፈትቶ የሚያስለቅቅልን ተግባር ነው ።

## በቀን ህልም መጻፍና፤ መሞነጫጨር

እቤትም ሆነ ቢሮ፤ በስልክ መልዕክት ስትቀበል ወይም ስታስተሳልፍ ሁሌም ሰማለት ይቻላል፤ ስክሪፕቶ የማይለይህ መሆኑን ልብ ብለኸዋል? ምናልባት ቀጠሮህን በአጀንዳ ላይ ትመዘግብ ይሆናል ወይም ወዳጅህን የምትጠይቅበትን ቀን በመመዝገብ ላይ ነበርክ ማለት ነው ። ወይም አዲስ የገዛኸውን ልብስ ማጠቢያ ማሽን የምትረከብበት ቀን በመመዝገብ ላይ የነበርክ ትሆናለህ።እጅግ የሚገርመው ግን በስልክ ላይ ሆነህ እጅህ ስለማያርፍ በማስታወሻ ደብተርህ ወይም ከፊትህ በሚገኝ ወረቀት ላይ ልዩ ልዩ ቅርፅ፤ ጌጣጌጥ ፤ፊደሎች ምኑ ቅጡ፤ መከተብ ወይም መሞጫጨር ልማድህ ሆኗል ። ብታምነውም ባታምነውም ያ ያሳረፈ እጅህ የሚከትበው ወይም ‹‹ዱድል›› የሚያደርገው ሥራ በያዙኝ ልቀቁኝ ላይ የሚገኝ ታላቅ የምጡቅነት (ጂኒየስ) ምልክት ነው።

እስካሁን ያሉት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የአንድ ሰው ልኂቅ ብልህነት መስፈርት ‹‹ዱድሊንግ›› ለማድረግ በሚወስደው ጊዜ ነው ። እውነተኛው ልኂቅ ብልህ አንድ ፈሊጥ አለው። በሚቀርብለት ጹሑፍ ወይም በራሱ ማስታወሻ ጎንና ጎን ላይ ማስታወሻ ካላስቀመጠ አያስችለውም ።

ብዙዎቻችን በህይወታችን ኡደት ውስጥ ታላላቅ ሊባሉ ይችሉ የነበር አሳቤዎች ብልጭ ብለውልን ነበር ፤ ታዲያ ምን ያደርጋል! ማስታወሻ አንይዝም ፤ እነዚህ ድንቅ አሳቤዎች ለዘለዓለሙ ተንነው ጠፍተዋል! ያችን እንቁ ለመመዝገብ ራእዩ ኖሮን በጹሑፍ አቆይተናት ቢሆንና ዛሬ ማስታወሻችንን ገልበጥ ስናደርግ ብናገኛት ምንኛ በተደሰትን ነበር ?

መከተብ ወይም ‹‹ደዱሊንግ ›› ለመጪው ትውልድ ታሪክ ማቆየት ማለት አይደለም። ለመከተብ ስክሪፕቶህን የምታነሣው በቀን ህልም ውስጥ ስትገባ ነው ፤ ለዚሁ ነው

ወዘተ እየተጠዘጠዘ ከመሆኑም በላይ ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር የመነጋገር መስተጋብርንም እየተማሩ ነው።

ግብረ መልስ የተግባር መልስ ነው ። መጽሐፍ በማንበብ ብቻ ጎማ መቀየርን ልትማር አትችልም ፤ አንዳንዴም እጅህ መቆሸሽ አለበት። መኪናዋን በክሪክ ማንሳት የተነፈሰውን ጎማ አውጥተህ ስኮርቱን (ትያሬውን) ለውጠህ ቡሎኖቹን አጥብቀህ መኪናው መሬት መመለሱን እንዴ ከተማርከው፤ ሌላውንም በትክክል ለማስተማር የሚያስችል ብዙ ግብረ መልስ አግኝተሀል ማለት ነው። ጎማ መለወጥ የሚባል ነገር ከእንግዲህ እንግዳ አይሆንብህም።

## የገላጭ ሃተታ ኃይል

ብልህነትህን ለማግዘፍ የአእምሮ እይታ ወሳኝ ሚና ይጫወታል ። ማናቸውንም አዲስ ክህሎት ለመማር የአንዘባውን ድርሻ የያዘው እሱ ነው፤ ክህሎቱ የማስታወስ ችሎታን በማሻሻል ወይም በራስ መተማመንን ከፍ ማድረግ ላይ ያነጣጠረ ሊሆን ይችላል ።

አንድን ነገር እያዩ ስለሱው ገላጭ ሃተታ መስጠት ትኩረትን የሚስብ ነው ። በአእምሮም ሆነ በአካል የምናየውን ነገር በገላጭ ሃተታ እያብራራነው እንደመሄዳችን መጠን አዳዲስ ዝርዝር ሁኔታዎች እየታዩን ይሄዳሉ ። ስለዚህ ስለ አንድ ነገር ገላጭ ሃተታ መስጠት ራሱ የአገላለፅ ኃይል ከመስጠቱም ባሻገር ገለፃውንም በትክክለኛነትና በዝርዝር ያስቀምጠዋል።

ስለ አንድ ነገር በከፍታ ድምጽ ገላጭ ሃተታ መስጠት ወዲያዉኑ ግብረመልስ የሚሰጥ ከመሆኑም ሌላ የአገላለፅ ኃይልህን በበለጠ ያጠናክርልሃል። በገለፃህ ውስጥ ህዋሳዊ መረጃዎችን እያበራከትክ የአእምሮ እይታህ እየተጠናከረ ይሄዳል፤ የብልህነት ደረጃህም በቶሎ እያደገ ይመጣል።

# ክፍል አምስት

## የቃላት አስማታዊ ኃይል

ከታሪክ ማህደር የተዋወቅናቸው ምጡቃን ድብቅ የፈጠራ ችሎታቸውን ለማስማራትና ፤ ብልህነታቸውን ቀስቅሰው አዲስ የከፍታ ክብረወሰን ለማስመዝገብ ሲንጠራሩ ፤ የአእምሮ እይታ ጥበብን የቱን ያህል እንደተጠቀሙበት ልናይ እንችላለን ። የአእምሮ ስዕሎችን በሃሳብ ከመዘከር ይልቅ ሙከ ባለ ድምፅ ስለነሱ ገለፃ ማድረግ የበለጠ እውነታን ሊያላብስ ይችላል። በመሆኑም ቃላት የአእምሮ እይታችንን ጥልቀት፤ ቅርፅ፤ ቀለም፤ ልስላሴ (ሻካራነት) ወርድና ርዝመት ሊያከሉበት የሚችሉ ቁልፍ መሣርያዎች ናቸው ።

የአእምሮ ስዕሎችን ምን ዓይነትነት የምንነልፅበት ቃላት ባይኖሩን ኖሮ ምናልባትም ሥዕሎቹ ራሳቸው በጠፉ ነበር ። በእርግጥ "የምናብ እይታ" (ኢማጂኔሽን ) ድንቅ ነገር ነው፤ነገር ግን ራዕይን በንግግር የመቅረፁ ችሎታ ነው መዋቅርና ትርጉም የሚያላብሳቸው።

ቃላት ከሰዎች ጋር የምንነጋገርበትን ቋንቋና መስተጋብር የማካሄድ ክህሎትን አስጨብጠውናል። ነገሮችን ሳንሰይማቸው ከነሱ ጋር የሚሄዱ ቃላትን ፍለጋ እንኳድም ። በአካባቢያችን የሚገኙትን ክስተቶችን ረጅም ጊዜ ወስደን ካጠናቸው በኋላ መለያ ምልክት እንለጥፍባቸዋለን ።

ብልህነትን ለማንሳበት በምትነሳሳበት ጊዜ የሚያጋጥምህም ይኸው ነው። የቃላትን ጠቀሜታ በቀላሉ ማየት ባያስፈልግም፤ ልትዘነጋው የማይገባው ቅደም ተከተላቸው መጀመሪያ ስዕል ቃላት ለጣቂ መሆኑን ነው። የአእምሮ እይታህን ህይወት ለማላበስ በቃላትህ ተጠቀም፤ይህንንም የምታደርገው የምናብ እይታህን ስታብራራ ብቻ ነው።

### ቃላት ይናገራሉ

እእምሮአዊ እይታህን በግምት ውስጥ ስታስገባ በአእምሮህ ስዕሎችህ ውስጥ የሚኖረውን ትርጉም ለመግለጽ የሚቻለው በቃላት ብቻ ነው ብሎ ለመደምደም የሚዳዳቸው ሰዎች

በአንድ በተወሰነ ጊዜ የምናቀርበው ጥያቄ በእርግጥ የሚበጀን (የማይበጀን) መሆኑን እንዴት ልንገነዘበው እንችላለን? ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት የፈጠራ ችሎታችንና የምናብ እይታችን ህዋሶች ተሸክፈው ወደ ሚኖሩበት የአንጎላችን ጓዳ ፤ ማለትም ወደ ስውር አእምሯችን ፤ የምንገባበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርብናል ማለት ነው ። ንቁ አእምሯችን ጉዳዩን በጥንቃቄ ከመረከቡ በፊት ፤ ወዲያው መልስ ለሚሹ አጣዳፊ ጉዳዮች ተጠያቂው ስውር አእምሯችን ነው ።

## ለስውር አእምሮ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ስውር አእምሮን ለመቀስቀስ መደረግ የሚገባው ተግባር እኩል በተቆረጠ አንድ ዓይነት ቀለም ባላቸው እያንዳንዳቸው ባዶ ወረቀት ላይ የተጻፉ ጥያቄዎችን አቅርብ። በአጭበርባሪነት እንዳትታማ የወረቀቶቹን እኩል መቆረጥና አንድ ዓይነት ቀለም መሆናቸውን አጣራ ። ወረቀቶቹ ጽሑፋቸው እንዳይታይ ገልብጠህ ፕውዛቸውና አንዷን በአቦሰጡኝ ምዘዛት ።

ከዚያ በኋላ በወረቀቱ ላይ የተጻፈውን ሳታይ ዓይንህን ጨፍንና ጥያቄው ምን እንደሚል ገምት። የአእምሮ እይታ ክህሎትህን በማንቀሳቀስ በወረቀቷ ላይ የተጻፈውን ጥያቄ በአእምሮ ውስጥ "ለማየት" ጥረት አድርግ።

አንድ ዓይነት የአእምሮ ሥዕል ከቀረጽክ በኋላ፤ ዓይንህን ግለጥና ወረቀቷን ገልብጣት። ጽሑፉን ከተመለከትክ በኋላ ጥያቄው ከአንተ "ምናባዊ እይታ" ከተከሰተልህ ጥያቄ ጋር የቱን ያህል አግባብነት እንዳለው መርምር ።

ጥያቄዎችን የፃፍካቸው አንተው ራስህ በመሆንህ ስለምታውቃቸው፤ ቴክኒኩ ይሠራል ማለት ነው። የማታውቀው ነገር ቢኖር ከጥያቄዎች መካከል የትኛው ነው በቅድሚያ መልስ ሊሰጠው የሚገባ የሚለው ነው።እሱንም ቢሆን ስውር አእምሮህ ስለሚያውቀው ትክክለኛውን መልስ በመስጠት ረገድ እገዛ ሊያደርግልህ ይችላል።

## የሂሳብ ፕሮብሌሞችን በፍጥነት ለመፍታት 10'ን መፈለግ

ቁጥሮች ወደ አስር ሲጠጋጉ ወይም የአስር ብዜት ሲሆኑ 10 (20፣30፣40 ወዘተ) ቁጥሮችን መስራት (ማስላት) ቀላል እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። ይህንን እውቀት ተጠቅመን ቁጥሮችን በማጠጋጋት እና ግምት በማውጣት በፈጣን እና ቀለል ባለ መልኩ ቁጥሮችን ማስላት እንችላለን። ለምሳሌ 97 ቁጥር ለመቶ የተጠጋ ነው11 ቁጥር ደግሞ ለአስር የተጠጋ ነው። 53 ቁጥር ደግሞ ለ 50 የተጠጋ ነው። እነዚህን ቁጥሮች በአንድነት ለመደመር እንደሚከተለው ቁጥሮችን በማጠጋጋት በቀላሉ መገመት እንችላለን

97 ሲጠጋጋ 100

11 ሲጠጋጋ 10

53 ሲጠጋጋ 50

እንደምትመለከቱት በቀኝ በኩል ያለው ረድፍ ቀለል ያለ ሲሆን ሁሉንም በአንድነት በፍጥነት መደመር እንደሚቻል ትረዳላችሁ። የመጀመሪያ ቁጥር እስከ 161 ይደመራል፣ የተጠጋጋው ቁጥር ግን እስከ 160 ይደመራል። ያም ለግምት በጣም የቀረበ ነው፤ አያስብልህም?

### ወደ መቶ ማጠጋጋት

ይህን ዘዴ በመጠቀም ደግሞ ወደ መቶ የሚጠጉ ቁጥሮችን ማባዛት እንድትችል የሚረዳህ ነው። በተለምዶ 97 እና 92 በአንድነት ማባዛት አደናጋሪ ነው ብለህ ታስብ ይሆናል። ነገር ግን በዚህ ዘዴ በጣም ቀላልም ሊሆን ይችላል። መስራት ያለብህ ግን እንደሚከተለው ነው።

መጀመሪያ መቶን ለማግኘት እያንዳንዱን ቁጥር አጠጋጋው። ከዚያም ቁጥሩን መቶ ለማድረስ ምን ያህል ቁጥር መደመር እንዳለብህ አስብ። 97 ወደ መቶ ሲጠጋ 3ን ይወስዳል። 92 8ን በመውሰድ 100 ይሆናል።

97 (3)

92 (8)

አሁን በግራ በኩል ያለውን አንዱን ቁጥር በቀኝ ካለው አንድ ቁጥር ጋር በአግድሞሽ ቀንሰው። ለምሳሌ 92-3 = 89. አሁን ይህ ያገኘነው ውጤት (89) የመልስህ የመጀመሪያው 2 አሃዞችን ይመሰርታል። ቀጥሎ ያለው ሂደት ደግሞ ሁለቱን ነጠላ ዲጂት ቁጥሮች በአንድ ላይ ማባዛት ነው። ይኸውም 3x8=24. ይህም ማለት የመልስህ የመጨረሻዎቹ ሁለት አሃዞች ይሆናል ማለት ነው። ሁሉንም በአንድነት

11<br>42<br>+57<br>110

መልስህን ለመረጋገጥ ከታች ወደ ላይ እየቀነስክ ሂድ

110<br>-57<br>53<br>-42<br>11

የመጨረሻው መልስ ከመጀመሪያ ቁጥር (11) ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ በእርግጥ መልሳችን ትክክለኛ መሆኑን የምናውቅበት አንዱ መንገድ ነው።

<u>11 የሚመች ቁጥር ነው</u>

ዘጠኝና እና አስርን ስለጨረስን አሁን የሚያጓጓን 11 ቁጥር ላይ ደርሰናል። አንድ ቀላል አሰራር በመጠቀም እና በጥያቄው ውስጥ ምን ያህል ዲጂቶች እና ቁጥሮች እንዳሉ አይተን ማስተካከያ በማድረግ ማንኛውንም ቁጥር በ11 ማባዛት እንችላለን። ይህንንም የክፍተት እና የመደመር ፅንሰ ሃሳብ እንለዋለን። ይህም ለምን እንደሆነ ቀጥሉ ትመለከታለህ ! ለሁለት ዲጂት ቁጥሮች ማድረግ ያለብህ እንደሚከተለው ነው።

11 ን በ15 ለማባዛት ፈልገናል እንበል።15 ቁጥርን ውሰድና በእንዲህ ዓይነት መልኩ በመሀከላቸው ክፍት ቦታ እንዲኖር አድርግ 1 5. አሁን እነዚህን ቁጥሮች መልሰህ ደምራቸው (1+5=6) የድምሩን ውጤት ወስደህ በክፍቱ ቦታ አስቀምጠው። ያም 165 ቁጥርን ይሰጥሀል ማለት ነው። ቀላል አይደል?
ሶስት ዲጂት ቁጥሮችን በ11 በምታባዛበት ጊዜም ሂደቱ ተመሳሳይ ነው። ለማብራራት 123 ቁጥርን እንውሰድ፤ አሁን ግን የክፍቱን ቦታ በመጀመሪያው እና በመጨረሻው ቁጥር መካከል
1 3 በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ እናስቀምጠዋለን። ቀጥለንም የመጀመሪያዎቹን ባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮችን በአንድነት እንደምራቸዋለን (1+2 = 3) ከዛም የመጨረሻዎቹን 2(ሁለት) አሃዝ ቁጥሮች በአንድነት እንደምራቸዋለን (2+3=5) እነዚህን ቁጥሮች ውሰድና በቅደም ተከተላቸው (ማለትም ከግራ ወደ ቀኝ) አስቀምጣቸው። ያም ማለት

የበለጠ ስለሆነ 27 የመጀመሪያ ቁጥርህ ይሆናል ማለት ነው። ሁለተኛው ቁጥር 21 ሲሆን ይኸም ከ100 ያነሰ ስለሆነ 21 ሁለተኛው ቁጥርህ ይሆናል ማለት ነው። አሁን ቀጥሎ እንደምትመለከተው ሁለቱን ቁጥር ደምራቸው 27 + 21 = 48. መልሱም 127 - 79 = 48'ን ይሰጥናል።

በዕሁፍ መልክ የቀረበ የመቀነስ ሂሳብ ቢቀርብልህ ከዚህ በፊት የተመለከትናቸውን አንዳንድ ዘዴዎችን በመጠቀም ከመቅፅበት መልሱን ማግኘት ትችላለህ! ለዚህም ይረዳህ ዘንድ ከሺህዎች ጀምረህ፤ ትንሹን ቁጥር ከትልቁ መቀነስና እንደሚከተለው አድርገን መስራት እንችላለን፤

  7254
- 3897

መፍትሔ: 7254 - 3000 = 4254

4254 - 800 = 3454

3454 - 90 = 3364

3364 - 7 = 3357

ወይም በማጠጋጋት እና በመደመር እንደሚከተለው መስራት ይቻላል።

መፍትሔ: 7254 - 4000 = 3254 ልዩነቱን በ3897 እና 4000 መካከል እንደምር (103) 3254 + 103 = 3357

## በመደመር የመቀነስ ውጤትን ማረጋገጥ

መቀነስ የመደመር ተቃራኒ ነው የሚባለው ሌላው ማረጋገጫ መንገድ ሁለት ቁጥሮችን መቀነስ እንዳለብህ ባወቅህ ጊዜ፤ ለምሳሌ ከ57 ላይ 33 ቢሆን እንደሚከተለው ወደ ታች ፃፋቸውና እራስህን እንዲህ ስትል ጠይቅ፤-

57

-33

ለአስረኛው ረድፍ 3 ላይ ምን ቁጥር ቢጨመር ነው 5 የሚሰጥህ? መልሱ በእርግጥ 2 ነው።ለአንደኛው ረድፍ ደግሞ 7 ቁጥርን ለማግኘት 3 ቁጥር ላይ ምን ቁጥር መጨመር አለበት? አሁን ደግሞ መልሱ 4 ነው። ለ57 ትክክለኛው መልስ 33ን ስትቀንስ መልሱ 24 ነው።

ተብሎ ሊተነተን ይችላል እናም ይህን ቁጥር በ3 ወይም በ6 ማካፈል አይቀልም? ስለዚህም የማካፈል ስራችንን ቀለል እንዲያደርግልን ይህንን የመተንተን ዘዴ እንጠቀማለን። አሁን ስራችንን 486ን በ18 በማካፈል እንጀምራለን

የመጀመሪያው ስራችን 18ን 3 እና 6 ብለን በአካፋዮቹ መከፋፈል ነው። ከዚያም ለመጀመር ያህል 486 ን ከሁለቱ በአንደኛው ትናንሽ ቁጥሮች እናካፍለዋለን።

```
     81
6 / 486
    48
     6
     6
     0
```

48 ሲካፈል ለ6 ስምንት ጊዜ ይሆናል ። አስብ፤ ምን ያህል ጊዜ ነው 6 48ን የሚሰጠን። መልሱ ስምንት ጊዜ ነው። ከዚያም 6 ሲካፈል ለ6 አንድ ጊዜ ይሆናል። ስለዚህ የመጀመሪያው የማካፈል ስራህ 81 የሚል መልስ አምጥቶልሀል።

አሁን ደግሞ መልሱን ለማግኘ አንድን (81) በሌላው የ18 አካፋይ በ3 እናካፍለዋለን። እናም እንደቅድሙ ስራችንን እንቀጥል፤

```
     27
3 /  81
     6
     21
     21
      0
```

ስምንት ሲካፈል ሶስት ሁለት ጊዜ ሆኖ ሌላ ሁለት ቀሪ ነበረን፤ ያም ቀሪውን ቁጥር 21 አምጥቶልናል ይህም 21 ሲካፈል ለሶስት ሰባት ጊዜ ይሆናል ማለት ነው መልሱም 27 ነው።

ምክንያቱም የመጀመሪያውን ቁጥር በ6 አካፍለነው 81 የሚል መልስ ስለሰጠን ቀጥለንም 81ን ለ3 ስናካፍለው 27ን ሰጥቶናል። ከሁሉም ቁጥሮች ጋር ስለስራን

የመጨረሻው መልሳችን 27 ሆኗል፤ ይህም የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ነው፤ 486 ሲካፈል ለ18፡፡

## የዕለት ተዕለት ሂሳባዊ መፍትሔዎች፤ ፈጣን መመንዘሪያዎች

በቤትህ ወይም በቢሮህ ሆነህ ይጠቅሙኛል የምትላቸውን የአየር ንብረትን እና አንዳንድ መለኪያዎችን በፍጥነት የምትለውጥባቸው ዘዴዎች ቀጥለው ቀርበውልሃል፡፡

### የሴልሲየስ እና የፋራናይት መቀየሪያዎች

ሲልሲየስን ወደ ፋራናይት ለመቀየር በ1.8 አባዝተህ 32 መደመር ነው፡፡ ለምሳሌ 33 ዲግሪ ሴልሲየስን ወደ ፋራናይት ቀይረው ብትባል መልሱ 33x1.8 = 59.4 + 32 = 91.4 ሲሆን ሲጠጋጋ 91 ይሆናል፡፡ ለፈጣን ግምት በ2 አባዝተህ 30 መደመር ነው፡፡ ለምሳሌ 10 ዲግሪ ሲልሲየስ ሲባዛ በ2 20 ሲሆን፤ ሲደመር 30 መልሱ ሃምሳ ዲግሪ ፋራናይት ይሆናል፡፡

ፋራናይትን ወደ ሲልሲየስ ለመቀየር ማድረግ ያለብህ 32 ቀንሰህ 1.8 ማካፈል ነው፡፡ ስለዚህ 75 ዲግሪ ፋራናይት ወደ ሲልስየስ ሲቀየር ይህን ይመስላል 75 - 32 = 43 ሲካፈል በ1.8 = 23.8 ሲሆን ሲጠጋጋ 24 ይሆናል፡፡

መልሱን ለመገመት ያህል በ30 ቀንሰህ በ2 ማካፈል ነው ወይም ቁጥሩን ለሁለት ማካፈል፡፡ ለምሳሌ ከ66 ዲግሪ ፋራናይት ላይ ሰላሳ ስንቀንስለት ቀሪው 36 ሲሆን ይህ ለሁለት ሲካፈል 18 ይሰጠናል፡፡ ወይም 18 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ማለት ነው፡፡

### ወደ ሜትሪክ መቀየር

1 ማይል=1.6 ኪሎሜትር ነው፡፡ ኪሎሜትርን መልስን ወደ ማይል ለመቀየር ዘዴው በ6 አባዝቶ የመጨረሻውን ዜሮ ማስወገድ ነው፡፡ ለምሳሌ 15 ኪሎሜትር 9 ማይል ይሆናል፡፡ ምክንያቱም 1.5 x 6 = 90 ዜሮን ስናስወግድ 9 ቀረን ማለት ነው፡፡

1 ኩባያ = .24 ሊትር ነው፡፡ ይህም ወደ ሩብ የተጠጋ ሲሆን ከመረጥክ ስራህን በዚሁ መቀጠል ትችላለህ፡፡ ወይም የበለጠ ትክክለኛ መልስ ከፈለክ ካልኩሌተር በመጠቀም የልኬትህን ውጤት ታገኛለህ፡፡ ይህ መጠንን ከኩባያ ወደ ሜትሪክ ወይም ከሜትሪክ ወደ

ኩባያ ስንቀይር የምንጠቀምበት ምቹ ዘዴ ነው። ሶስት ኩባያ ዱቄት ወደ ¾ የተጠጋ ሊትር ማለት ነው እናም አንድ ሊትር ከአራት ኩባያ ጋር እኩል ለመሆን ይቃረባል።

"ክፍልፋዮችስ እንዴት ሊሆኑ ነው?" ልትል ትችላለህ፣ ½ ኩባያ ስኳር ፈልገሃል እንበል። አትጨነቅ! ማድረግ ያለብህ ክፍልፋዮችን ወደ ዴሲማሎች 0.5 መቀየር እና 0.24 ማባዛት ነው። ወይም አንድ ኩባያ የአንድ ሊትር ሩብ እኩያ ነው ብለህ ከተነሳህ ግማሽ ኩባያ ደግሞ የሊትር የሩብ ግማሽ (1/8) ጋር እኩል ነው ማለት ነው።

## ኩባያዎች እና ጆጎች

በድሮ ጊዜ ብዙ የወጥ ቤት ሰራተኞችን የሚያደናግር ነገር ይኸውላችሁ። ለምግብ አሰራር መስፈረያ የሚሆንህን አንድ ኩባያ ውሀ ልትለካ ፈልገሀል እንበል። ነገር ግን ያለህ ኩባያ/ጆግ ግን ባለሶስት እና ባለአምስት ኩባያ ነው እንበል። ምን ታደርጋለህ? እነዚህን ሁለት ጆጎች እንዴት ብትጠቀምባቸው ነው ትክክለኛውን አንድ ኩባያ ውሃ የምታገኘው?

ማድረግ የሚጠበቅብህ ሶስቱን ኩባያ አንዴ በውሃ ከሞላኸው በኋላ ወደ 5 ኩባያው መያዣው ጆግ ላይ ትገለብጠዋለህ። ከዚያም እንደገና መልሰህ ሶስት ኩባያውን በውሃ ትሞላ እና ወደ አምስት ኩባያ ትገለብጠዋለህ። ከዚያም እጅህ ላይ ያለው ኩባያ አንድ ኩባያ ሆነ ማለት አይደል።

የባርክ ሙዚቃ ዓይነቱም ቢበዛ፣
ሁሉም በየፈርጁ አለው ልዩ ለዛ፡፡
የባርክ ሙዚቃ እኔ ምወዳቸው ፣
ሚኒዌት ሳራባንድ ይባላል ስማቸው
ጋቮትና ጊግም ከዚያው ወገን ናቸው ፡፡
ሚኑዌት እማይፈጥን ባለሶስት ምት፤
ባልና ሚስት አብረው እሚደንሱት፡፡
ዳንሱን ሲጀምሩ እሃዱ ብለው ፣
ጥንድ ጥንድ ሆነው በሚኑዌት ነው ፡፡
ሳራባንድ አይፈጥንም እጅግ ዘገምተኛ
የተቀመረ ነው ላዳዲስ ፍቅረኛ፡፡
ቀኝ እጇን በግራው ጨብጦ አድርጓት ፤
እንገቱና እንገቷ ፈጥረው ንክኪት፤
በሳራ ባንድ ነው የሚደንሱት ፡፡
ለድግሱ መዝጊያ የሚቀርበው ጋቮት፣
ወጣቱ የሚደፍረው የሚጠይቅ ጉልበት ፣
አዛውንት የሆነ አይሞክር ይቅርበት
ጊግ ቢያሽከረክርም የደስ ደስ አለው
አዛውንት ሞክሩት ምንም ክፋት የለው፡፡

ከፍተኛ ምኞት ያለህ ከሆንክ ደግሞ በየሳምንቱ ልዩ ልዩ የማስታወሻ ሀይልን የሚያጎለብቱ ዘዴዎችን ለምን አትሞክርም? ከምህጻረ ቃል ዘዴ ጀምረህ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ተጠቀምባቸው ::ልዩ ልዩ ትውስታዎችን እየቀሰቀስክ ከመሄድህም ባሻገር ከመረጥካቸው የማስታወስ ሀይል ከሚያጎለብቱ ዘዴዎች የትኛው እንደሚመችህና የትኛው ችግርህን እንደሚፈታልህ ለይተህ ልታውቅ ትችላለህ ::

# ክፍል ስምንት

## የአእምሮ ካርታ

የአእምሮ ካርታ የተሰኘው ስርንቀል የአትድ አዘገጃጀትና የማስታወሻ አያያዝ ስርዓት በመላው ዓለም የሚገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት የቀየረ ዘዴ ነው። የአእምሮ ካርታ አነዳደፍ ዘዴ ያቀረበው የጥበቡ ፈልሳፊ የሆነው ቶኒ ቢውዛን ራሱ ነው።ይህቺ አነስተኛና ተግባራዊ የሆነች መመሪያ ቀጥሎ የተመለከቱትን ተግባራት እውን ለማድረግ የምትረዳን ናት፡፡

የተማርነውን ትህምርት በቀላሉ እንድናስታውስ

ንግግር ወይም ዘገባን እንድናቅድ

ብሩህ አሳቤዎችን እንድናመነጭ

ሰዎችን አሳምነን ለመደራደርም እንድንበቃ

ቁምነገሮችን ለማስታወስ እንድንችል

የግል ግባችን በእቅድ ለመያዝ እንድንበቃ

በራስ ህይወት ላይ ቁጥጥር ማድረግ እንድንችል ትረዳናለች፡፡

የአእምሮ ካርታ ማለት አንድ ቃል ወይም ሃሳብን ማዕከል አድርጎ ከዚያ ተነስቶ ያች ማዕከላዊ ቃል ወደ ጠቆመችው ተዛማጅ ቃላት ወይም ከሷ ጋር ተመሳሳይነት ወዳላቸው ቃላት የመዝለቅ ስልል ነው ፡፡ አንዳንድ ምንጮች ደግሞ ከብስክሌት ጎማ ደጋገል (axel) ተነስተው ወደ ዳር የሚሰራጩ ሽቦዎች ጋር ያመሳስሏቸዋል ፤ ይህ ምሳሌ ነገሮችን እጅግ የሚያቃልል ሁኖ ስላገኘነው እምብዛም ግምት የምንሰጠው አይሆንም፡፡ እውነተኛ የአእምሮ ካርታ የሚጠቀምባቸው ቃላት ብቻ ሳይሆኑ ስዕሎችን፣ ቀለሞችን፣ ጮጭርጭር መስመሮችን፣እንዲያውም የካርታ አንሺውን የፈጠራ ችሎታ ሊያሥፋፋለት የሚችሉትን መገልገያዎች ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ በእንግሩም ምንም ዓይነት ቃላት ሳይጠቀሙ በስዕሎች ብቻ የአእምሮ ካርታ ለመስራት ይቻላል ፡፡

ብሩህነትን በማጎልበት መሳሪያነቱ የአእምሮ ካርታን እጅግ ጠቃሚ የሚያደርገው፤ አንድን ሰው ብሩህ (ምጡቅ) የሚያደርጉትን ልዩ ልዩ ባህርያት ሁሉ በአንድ ቴክኒክ



a




FRUIT
ORANGE
VITAMIN C
CITRUS
JUICE
APPLE
DOCTOR
AWAY
EYE
PIE
BANANA
YELLOW
CARIBBEAN
POTASSIUM
CHERRY
BLOSSOM
STONES
ORCHARD
PINEAPPLE
TROPICAL
SPIKY
COCKTAIL


GIFTS
MOTHER
HOBBIES
GARDENING
SEWING
FABRIC
HIKING
BOOTS
LIKES
OPERA
CDs
TICKETS
RADIO
DISLIKES
CHOCOLATE
MUSIC POP
TELEVISION
FATHER
HOBBIES
GOLF
BALLS
CLUBS
TENNIS
RACQUET
WHITES
LIKES
MUSIC CLASSICAL
CDs
TICKETS
PHOTOGRAPHY
CAMERA
DISLIKES
TRAVEL
SISTER
LIKES
WINE
MUSIC
ROCK
READING
HOBBIES
YOGA
MAT
CLOTHES
PAINTING
ANIMALS
DISLIKES
JAZZ
SPORT
SON
HOBBIES
GAMES
CONSOLE
TRAINS
SET
LIKES
FOOTBALL
DISLIKES
DAUGHTER
HOBBIES
KARATE
DRAWING
PENCILS
LIKES
MUSIC
POP
POSTERS
CDs
TICKETS
CONCERT
CLOTHES
JEANS
COAT
DISLIKES
DRESSES
MUSIC
RAP


STARTING A NEW VENTURE
AIMS
PERSONAL
FINANCIAL
EMPLOYEES
PARTNER
STAFF
FAMILY
ADVERTISE
INTERVIEW
IDENTITY
NAME
LOGO
DESIGN
STATIONERY
LOCATION
MOBILE
PROPERTY
HOME
RENT
BUY
DECORATE
CUSTOMERS
NEAR
PLENTY
MARKETING
CUSTOMER
RESEARCH
ADVERTISE
WEBSITE
RADIO
MEDIA
NEWSPAPER
WORD OF MOUTH
DISPLAY
POSTERS
LEAFLETS
NOVELTY
PROMOTIONAL OFFERS
FINANCES
BUSINESS
PLAN
CONSULT
BANK
ADVISOR
INVESTORS
BUDGET
COSTS
CAPITAL



FAMILY EVENTS
MONDAY
FATHER BUSINESS MEETING
CHILDREN SWIMMING
TUESDAY
DAUGHTER LESSON PIANO
SON EXAM
MOTHER YOGA
WORK PRESENTATION
WEDNESDAY
DOG VET
DINNER PARTY
THURSDAY
FATHER MATCH TENNIS
DAUGHTER LESSON DANCE
SON HAIRCUT DENTIST
FRIDAY
PARENTS PARTY
CHILDREN BABYSITTER
SON FOOTBALL
SATURDAY
GUESTS ARRIVE
SHOPPING FOOD
SUNDAY
FAMILY


SURPRISES
LOCATION
TRAVEL
EQUIPMENT
ACTIVITIES
DINING

# ክፍል ዘጠኝ

## ኒ.ሊ.ፒ. ካሪስማ (የስበት ሃይል ያለው)፣ግንኙነት እና ስኬት

ምጡቅ መሆን አንድ ነገር ነው። ከመክሊትችን አጅግ ብልህ የተባለው ሰው ቢሆን ፣ ከሌሎች ጋር ግንኙነት መፍጠር ይኖርበታል። አንድ ሰው የከፍተኛ ክህሎት ባለቤትና ከፍተኛ ምሁር ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን በህዝብ ዘንድ ካልታወቀና ብቃቱንም በስራ ካላስመሰከረ የዚያ ሰው ጠቀሜታ የቱ ላይ ነው? ያለህ የአእምሮ ብቃት ምንም ይሁን ምን፤ " የህዝቡ" ሰው መሆን ይኖርብሃል።

በአንድ ፓርቲ ወይም ዝግጅት ላይ የሰውን ሁሉ ትኩረት ለመሳብ ብትችልና የምትናገረውን ለማድመጥ በዙርያህ ብዙ ሰዎች ቢኮለኮሉ ድንቅ የሚያስብል ነገር አልነበረም? ኒ. ሊ. ፒ (Neuro Linguistic Programming) የተባለውን ጥበብ መሰረታዊ እውቀት ከጨበጥክ አንተ ራስህ ያን ሰውዬ የማትሆንበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ማግኔት ብረትን እንደሚስብ ሁሉ አንዳንድ ሰዎች ትኩረት የመሳብ ልዩ ተሰጥኦ አላቸው፡ እነሱ ሲናገሩ ሌሎች ያዳምጧቸዋል። ከሌሎች ጋር ቅጽበታዊ ግንኙነት የመፍጠር ልዩ ችሎታ አላቸው። ምስጢሩ ምን ይሆን?

እዚህ ላይ ቁልፉ ቃል "ግንኙነት" (rapport) የሚለው ቃል ነው፤ ግንኙነት ማለት ከሌሎች ጋር አይን ለአይን እየተያዩ መግባባትና በነሱው "የራዲዮ ሞገድ" በመጠቀም ግንኙነት መፍጠር ማለት ነው። የግንኙነት ክህሎትህን በቶሎ የምታሻሽልበት ቀላል ዘዴዎች እነሆ

- አዳምጥ! ሌላውን ሰው የሚያስደስተው ምን እንደሆነ አጥንተህ ድረስበት። እሱ ወይም እሷ እንዲናገሩ ፍቀድላቸው፤ ሙሉ ተሳትፎህ ያልተጓደለ አድማጭ ይሁን፣ ሌላውን የሚያስደስተው ምን እንደሆነ ለማወቅ ሞክር፣
- ሌላው የሚጠቀምባቸው ቃላትና አረፍተ ነገሮችን ካዳመጥክ በኋላ ራስህ በምትነጋገርበት ወቅት ተጠቀምባቸው፤

### የባህርይ ለውጥ

ሊትለውጠው የምትሻው ባህርይ ምንድነው? ለውጡስ በተለሳለሰና በተሟላ መልኩ ይፈፀም ዘንድ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

### ክህሎቶች

ያለምከውን የባህርይ ለውጥ ለማምጣት የሚፈለገው እውቀትና ክህሎት ምን መሆን አለበት? በሌላ አነጋገር፤ የምትሻውን ለውጥ እንዴት ነው የምታሳካው?

### የሚገፋፋ ኃይል (ሞቲቬሽን)

በእርግጥ፤ ያለምከውን ግብ ትመታ ዘንድ እንድትገፋበት ምኞቱንና ዕንአቱን የሚሰጡህ የራስህ እሴቶችና እምነቶች ናቸው፡፡ ለነገሩ ለለውጡ ይህን ያህል ግምት መስጠት ለምን አስፈለገ?

### የማንነት ግንዛቤ

እውን፤ ለውጡ ልትሆን የምትሻውን ሰው ያደርግሃል? ለነገሩ ማን ነህ አንተ?

### አመክንዮ

እስቲ ራስህን ሰፋ ባለ ማዕቀፍ ውስጥ ክተተውና ይህ ያለምከው ለውጥ ላንተ ያለው ጠቀሜታ የቱን ያህል እንደሆነ ገምግመው፡፡ የለውጡ የበለጠ ተጠቃሚ ማን ነው?

## የግብ መቆጣጠሪያ ሊስት

አንድ ሰው ለውጥ በመሻት የግብ ጉዞው መጀመሩ የዚያን ሰው እስደናቂ ፀባይ ከማንፀባረቁም በላይ፤ ራሱ የብልህነት መገለጫ ነው፡፡ ነገር ግን በግብ አቅጣጫ ጉዞህ እንዳደረክ የምታውቅበት ዘዴ ከሌለህ ሁሉም ነገር መና ሆኖ ይቀራል፡፡ ፈለግህን ጠብቀህ በትክክል የምትጓዝ መሆኑን ለማረጋገጥ አንድ መጠይቅ ዝርዝር አደራጅተህ በተፈለገው ጊዜ ካስፈለገ በየቀኑ አሊያም በየሳምንቱ ለረጅም ጊዜ ቁጥጥር እንድታካሂድ ያስፈልጋል፡፡

መሆን የምትሻውን ሰው ትሆን ዘንድ ለራስህ ግብ ማስቀመጥ የምትሻው ግብ አንዱ ክፍል ነው፤ ከዚህም ሌላ ልትደርስበት የምትሻውን ግብ ከወዲሁ ጥርት አድርገህ የምታውቅ ብልህ ሰው መሆንህንም ያረጋግጣል።

እንግዲህ ግብ ካስቀመጥክ ዘንዳ ግቢን መታሁ የምትለው ያንጣጠርክበትን "ዒላማ ስትመታ" ነው። በሌላ አነጋገር አንድን ነገር በተለመደው አሠራር ከሠራነው የተለመደው ውጤት ነው የሚሰጠን። መንገድህን ሳትስት ዓላማህን ጠብቀህና ግብህን ከአይታህ አቆራኝተህ ቀጥሎ የተመለከቱትን እርምጃዎች ተከተል፡፡

## ግብህን ለይተህ እወቅ

የምትፈልገውን ካላወቅህ፣ ልታገኘው ተስፋ የለህም ማለት ነው። የምትፈልገውን በትክክል እወቅ። ግብ አድርገህ የምትፈልገውን ዕቃ ሸካራነቱን፣ ልስላሴውን፤ ቀለሙን፤ ቅርፁንና፤ ስፋት-ጥበቱን ያሰብነውን በቱባው ለማግኘት የሚያስችለውን ባህርይ ሁሉ ዘርዝረህ ግለጽ።

## ወደፊት ዝለቅ

ግብህ ከተረጋገጠ ዓይነቱም በግልጽ ከተቀመጠ በኋላ ወደፊት መዝለቅ ነው ያለብህ። ለማናችውም ጅማሮህ በጥቂቱ መሆን አለበት ብንልም አካሄድህ ከማንሱ የተነሳ ወደግብህ የምታደርገውን ግስጋሴ አንድ እርምጃ እንኳ የማያስኬድህ መሆን የለበትም። ከዚህ በኋላ ደረጃ በደረጃ ወደፊት ዝለቅ።

## ንቁ ሆነህ ተገኝ

ግብ ለመምቻህ እንቅፋት የሚሆኑትንና የማይሆኑትን ከወዲሁ ማወቅ ስላለብህ ማናቸውም አማካይ ባህርዮቹን ሁሉ ይዞ መጓዙን አጣራ፤ ካላፈለገም ካሰምከው ግብ አካሄድ ጋር እርምጃህን ታስተካክል ዘንድ ከአንተ በኩል መለስተኛ የባህርይ ለውጥ መደረግ ይኖርበታል።

- መዝናናት ወይስ ራስን ማደስ ? በመሳሪያ የታጀበ ሙዚቃ የዘፈንን ያህል ልብ አይነካም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የፒያኖና የሃርፕ (በገና መሰል) ሙዚቃ ማዳመጥ መንፈስህን ሊያረጋብ ይችላል፡፡
- የግል ስሜትህን ተማመነው፡፡አንድ ሙዚቃ ደስ ካላሰኘህ ለምን ታዳምጠዋለህ? ደስ የማይል ወይም ሊገባህ የማይችል ሙዚቃ ጆሮህን "ከሚደፍረው" ይልቅ ፀጥ ብሎ መቀመጥ ይመረጣል፡፡
- ቶሎ ቶሎ ለውጥ! አንድ ነገር የማይሰራ መሆኑን ከተረዳህ በቶሎ መለወጥ አለብህ (በዚህ ረገድ የፋትቦል ክለብ አሰልጣኝን አርአያ ተከተል) ፡፡ ጧት ከእንቅልፍህ ስትነሳ በዓለም ዜና ላይ ከመደነቅ ይልቅ የሚያነቃቃህን ሙዚቃ መስማቱ የበለጠ ይበጅሃል፡፡ ማታ ደግሞ ከመኝታህ በፊት ለስለስ ያለ ሙዚቃ ማዳመጥን ልምድህ ብታደርገውስ?

ሙዚቃ የሚያሳድርብን ተጽእኖ አንዳንዴ ሳይታሰም የተፈታ ነው፡፡ ለምሳሌ ጠንካራ ሮክ ሙዚቃ ማዳመጥ መንፈስህን የሚያረጋብ ሊሆን አይችልም፡፡ ስዊንግ ወይም ዲስኮ ስታዳምጥ መደነስ እንደሚዳዳህ የታወቀ ነው፡፡ የባሮክ ሙዚቃ ያንድን ሰው መንፈስ ፀጥ ወዳለና ወደተረጋጋ መዝናናት ውስጥ የሚከት ኃይል ያለው ይመስላል፡፡

ጥቂት ሙከራ ካደረግህ በኋላ የሚስማማህን፣ የሚነሽንጥህንና የሚያዝናናህን ሙዚቃ እንደምታገኝ እርግጠኛ ሁን፡፡

እንደዚያው ሰውዬ ተቆጥረህ የምትታይ ስለሆነ መጀመሪያ በስውር አእምሮ ደረጃ፣ ቀጥሎም ከሰውዬው ከራሱ ተቀባይነት ታገኛለህ።

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ማስጠንቀቂያዎች ሊስት በጥንቃቄ አንብበህ ግንዛቤ ከጨበጥህ በኋላ የሚረሪንግ ጥበብን ልምምድ ልታደርግበት ትችላለህ። ፍሬ ነገሩን ከጨበጥክ በኋላ በምታውቃቸውም ወይም በማታውቃቸው ሰዎች ላይ ዘዴውን ሞክረው። ቅደም ተከተሉን እንዳትረሳ፦

<u>አተነፋፈስ፣ ድምጽ፣ እጅ አወራወር፡</u>

- የሰውዬውን ትክሻ ከፍ ዝቅ ማለት በጥንቃቄ ተመልከትና አተነፋፈስህን ከሱ እኩል አድርግ፣
- ድምጽህን ከሰውዬ ድምጽ ቅላጼ ፍጥነትና መጠን ጋር አስተካክል፣ ሲናገር ከፈጠነ አንተም ፍጠን፣ ካልፈጠን ግን ዝግ ብለህ የሱን ድምጽ ለማስመሰል ሞክር፣
- ሰውዬው ሲነጋገር እጁን የሚያንቀሳቅስ ከሆነ አንተም ይህንኑ አድርግ፣ (ኮፒ ልታደርገው ሳትሞክር)፣ እጁን ያጣምራል ወይም ጣቶቹን አሰግስጎ ከሆነ አንተም ይህኑ አድርግ፣
- በንግግሩ የትኛው የስሜት ህዋስ ነው በደበልጥ ጎልቶ የሚወጣው ? ዓይን ነው ? (ምን እያልክ እንደሆነ እያየሁ ነው) አንተም ይህንኑ አድርግ፣ ጆሮ ነው ? (እየሰማሁህ ነው) አንተም ይህንኑ አደርግ።
- ሰውዬውን አዳምጠውና ስሜታዊ ወይም ቀንጠኛ ቃል ተጠቅሞ እንደሆነ የዚህን ትርጉም ይግባህ። ለምሳሌ አንድ ሰው "ሥራው ደብሮኛል" ቢልህ የሚደብረው ምንድ ነው ብለህ ጠይቅ። ወይም አንድ ሴት "ሀሪፍ የእረፍት ጊዜ አሳለፍኩ" ብትልህ ሀሪፍ የሆነበትን ምክንያት ጠይቅ።

የሰዎችን ስሜታዊ አነጋገር ይዘት ምንነት ካጤንክና ሊደረግ የሚገባውን በራሳቸው አነጋገር ዘይቤ ተጠቅመህ ካደረግህ እነዚያ ሰዎች አንተ የምትፈልገውን ሁሉ ከማድረግ አይቆጠቡም።

## ቃላትን በሀይል እና በስሜት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

ቃላት ፋይዳ አላቸው፤ ምክንያቱም ስሜታችንን የምንገልጽባቸው ናቸውና። ስንደሰት፣ ሲከፋን፣ ሲደብረን፣ ስንፈነጥዝ ወዘተ ስሜታችንን ለመግለጽ እንፈልጋለን። ይህንንም ለማድረግ ቀላሉ መንገድ ደግሞ ቃላትን መሰንዘር ነው።

ቃላት ሊገልጹት የሚችሉ

- ጀንበር በውቅያኖስ አድማስ ውስጥ ስትጠልቅ የሚስተዋለው አስፈሪ እይታ፤
- ልጅ ሲወለድ የሚከሰተው ለማመን የሚያስቸግር ደስታ፤
- ሥራን በጥሩ ሁኔታ መከወን የሚሰጠው ግዙፍ ደስታ፤
- እጅግ ማራኪ የሆነ ጥቁር ፈረስ በሰፊ መስክ ላይ ሲጋልብ የማየት ድንቅ ትርኢት፤
- ተአምራዊ የሆነው የነጎድጓድ ብልጭታ የምሽቱን ሰማይ ለአንድ አፍታ ወለል ሲያደርገው ማየት፤

ቃላት ሥዕል ለመሳል ይችላሉ፤ የተረሳውን አስታውሰው ትዝታ ሊፈጥሩብን ይችላሉ፤ ከመደጋገሙ ብዛት ለዛውን ያጣ ተረትን አዲስ ጥልቀትና ቀለም ሊሰጡት ይችላሉ። የኩነቶች መቼና የት፤ የተናጋሪውም ማንነት ወሳኝነት ባይካድም፣ የአንድ ንግግር ትዝታ እንዲያስደስትህ ወይም እንዲደብርህ ለማድረግ ይችላሉ።

ቃላት ሌላም ተግባር አላቸው፤ ሊያግባቡ ይችላሉ። የምትሰነዝራቸውን ቃላት በብርቱ ጥንቃቄ መርጠህ ካቀነባበርካቸው፣ በማናቸውም አጋጣሚ ሰዎች ሙሉ ትኩረታቸውን ቸረውህ የሚያዳምጡህ ከመሆናቸውም በላይ ማንነትህንም ለማወቅ ይሽቀዳደማሉ። ከሰዎች ጋር በምትነጋገርበት ወቅት ብርቱ ስሜት ይዘት ያላቸውን ቃላት ተጠቀም፤ ይህን ስታደርግ ቋንቋህ የራሱ የሆነ ኃይል ያመነጫል፤ በስሜት የታጀበ፣ ሁሉም ሊያዳምጠው የሚገባ ኃይል።

- በፍጥነት ካነበብክ የምታነበውን ማስተዋል አይቻልህም። "ሐሰት" በደንብ ማስተዋል የምትችለው በፍጥነት ስታነብ ነው፤ የበለጠ የምታተኩረው ልዩ ጠቀሜታና አግባብነት ያላቸውን ነጥቦች ለይቶ የሚያውቀው በዚህ አጋጣሚ ነው።
- በፍጥነት የሚያነብ የትኩረት ደረጃው የወረደ ነው። "ሐሰት" በፍጥነት ስናነብ ኃይል እያሰባሰብን እና እያገኘን እንሄዳለን፤ በበለጠም ትኩረታችን ይጠናከራል።
- መካከለኛ ፍጥነት ያለው አንባቢ ከተፈጥሮ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ፣ ሊማሩት የሚገባ አዋጭነት ያለው አሰራር ነው። "ሐሰት" መካከለኛ የንባብ ፍጥነት ከተፈጥሮ ጋር የሚጣጣም አይደለም፤በአጭሩ የንባብ መማር ማስተማሩ ውስንነት ውጤት ነው። ሰው ምን ለመከወን እንደሚችል ያለንን ግላዊ እምነት (አቋም) መለወጥ የንባብ ፍጥነትን ሂደት ለመገንዘብ ይረዳል። ይህም አእምሮ ከአፍራሽ አመለካከት ነጻ በመሆኑ እርምጃህን ሊያሰናክለው ስለማይችል ለስኬታማነትህ አበረታች ሁኔታ ይፈጠራል።

## የዓይን እንቅስቃሴ

ይህችን መጽሐፍ በምታነብበት ወቅት አጠገብህ ተቀምጬ የሚከተለውን ጥያቄ አቀርብልህ እንበል፤ "ለመሆኑ አይንህ በምን ፍጥነትና አቅጣጫ የገፁን ወርድ እንደሚዘልቀው በጠቋሚ ጣትህ አማካይነት ልታስረዳኝ ትችላለህ"? ብዬ። አብዛኛው ሰው አንድን መስመር ተከትሎ ከግራ ወደቀኝ በዚግዛግ አቅጣጫ እያነበበ ገጹን እንደሚከተለው ይዘልቀዋል።



ህፃናት ንባብ ሲማሩ መጠቆሚያ ጣታቸውን ቀስረው መስመሩን ይከታተላሉ። ይህ ዘዴ የንባብ ፍጥነታቸውን ያቆረቁዘዋል በሚል የተሳሳተ ግምት ምክንያት ህፃናት በጣታቸው ንባባቸውን እንዲያነቡ አይበረታቱም። እንደእውነቱ ከሆነ፣ የንባብ ፍጥነታቸውን የሚያቆረቁዘው የጣት ጥቆማ ሳይሆን አደጋው ዝግታ ነው። ስለዚህ ህፃናት የሚያነቡትን በጣታቸው መከተሉን ሳይሆን መከልከል ያለባቸው ከትትሉን እንዲያፋጥኑ ነው መበረታታት ያለባቸው። በነገራችን ላይ ንባብን በጣት መከተሉ ጽሑፉን ሊያንሳቁሰው ስለሚችል በእርሳስ ወይም በእስኪርቢቶ መጠቀሙ ይመረጣል።

## ፍጥነት

አማካይ አንባቢ በግምት በደቂቃ ከ200 እስከ 240 ቃላት ሊያነብ ይችላል። ስናነብ ዓይናችን መረጃን ለመዝገን ሲፈልግ "እንጣጥ ይላል"፣ ያርፋል ወይም ካንድ ቃል ጋር ሙጥኝ ይላል። እነዚህን እንቅፋቶች አስወግዶ በቶሎ የንባብ ፍጥነትን ለማሻሻል ይቻላል።

## እንቅስቃሴ

ጽሑፎችን መስመር በመስመር እያነበቡ ማንዛቤ መጨበጥ ውጤታማ የሆነ ዘዴ መሆኑ ባይካድም እጅግ ፈጣን አካሄድ ግን አይደለም። ዓይናችን በገጽ ላይ ሲጓዝ ልዩ ልዩ ፈለጎችን ተጠቅሞ አሁንም መረጃን ውጤታማ በሆነ መልኩ ማጣጣም ይችላል።

ዓይናችን መረጃን ለማሰባሰብ ቆም የሚልበት እንደገናም ሂደቱን የሚቀጥልበት አካሄድ እንጂ በአንድ ገጽ ላይ ሳይቋረጥ ኮለል ብሎ የሚሄድበትን ሁኔታ የለውም። እጅግ የሚያስገርመው ደግሞ አይናችን መረጃዎችን ለመቅሰም የሚችለው መረጃዎቹን ረግተው ሲያገኛቸው መሆኑ ነው።

- አንድ ነገር ቀጥ ርግት ብሎ ከተገኘ ዓይንም ያን ነገር ለማየት "መርጋት" ባንድ ቦታ ላይ ማተኮር ይኖርበታል።
- በአንጻሩም አንድ ነገር በእንቅስቃሴ ላይ ካለ፣ ዓይንም ያን ነገር ለማየት መንቀሳቀስ ይኖርበታል።




(ምስል ሀ) የሚያመለክተው በንባብ ወቅት የአይን የመቆም እና የመነሳት ወይም የመዝለልን እንቅስቃሴ ነው።




(ምስል ለ) የሚያመለክተው አንድ ደካማ አንባቢ ባለመረጋጋት ምልከታ ሳይታወቀው እና ሆን ብሎ አንድ ቃልን እየደጋገመ ሲያነብ ነው።




(ምስል ሐ) የሚያመለክተው አንድ ቀልጣፋ አንባቢን የአይን እንቅስቃሴ ነው። በአንዳንዱ ምልከታ ብዙ ቃላት ሲዘነጉ እና የአይን ያለመረጋጋት ሳይታወቅ እና ሆን ብሎ መደጋገም መቀነሱንም ያሳያል።

1. ለይቶ ማወቅ

2. ማቀነባበር

3. ማገባቢ መጨበጥ

4. እውቀት

5. ማቆየት (መያዝ)

6. ማስታወስ

7. መልዕክት ማስተላፍ

**1. ለይቶ ማወቅ**

ማብራሪያ፡ የአንባቢ ፊደል የመለየት እውቀት ማለት ነው፡፡ ይህ እርከን ንባብ ከመጀመሩ በፊት የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡

**2. ማቀነባበር**

ማብራሪያ፡ "ከቃል ብርሃን የሚፈነጥቅበት ከዚያም ወደ ዓይን የሚደርስበት አካላዊ ሂደት" ሲሆን ከዚያም በአይታ ነርቭ አማካኝነት ወደ አንጎላችን ይተላለፋል ማለት ነው፡፡

**3. ማገባቢ መጨበጥ**

ማብራሪያ፡ "በንባብ የሚያጋጥመውን መረጃ ሁሉ አግባብነት ካለው ከሌላ መረጃ ሁሉ ጋር ማያያዝ" ማለት ሲሆን ይህም ቃላትን፤ ምስሎችን፤ ጽንሰ ሃሳቦችን፤ ስዕሎችን ወዘተ ያጠቃልላል፡፡ (ይህንንም በኔ አስተያየት "ኢንተግሬሽን" (ውስጠ-ውህደት) ብዬዋለሁ፡፡

**4. እውቀት**

ማብራሪያ፡ "አንባቢው ከዚህ በፊት ያከማቸውን እውቀት አሁን ከሚያነበው እውቀት ጋር እያማጣመ ተገቢውን ቅንጅት የሚፈጥርበት ሂደት ሲሆን ይኸውም መረጃን መተንተን፤ መተቸት፤ ማድነቅ፤ መምረጥ እና ውድቅ ማድረግን ያካትታል፡፡ በእኔ አስተያየት ይህ "ኤክስትራ ኢንተግሬሽን" (ተጨማሪ ውህደት) ብዬዋለሁ፡፡

5. ክምችት

ማብራሪያ፡ መሠረታዊ የመረጃ ክምችት በራሱ ችግር ሊሆን ይችላል፡፡ ብዙ አንባቢዎች በፈተና ጊዜ ለሚደርስው ስጋትና ጭንቀት ባይተዋር አይደሉም፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚፈለገውን መረጃ በወሳኙ የፈተና ወቅት ማስታወስ ስለሚሳናቸው ነው፡፡ ክምችት በራሱ በቂ አይደለም በማስታወስ መታጀብ አለበት፡፡

6. ማስታወስ

ማብራሪያ፡ የሚፈለገውን መረጃ በሚፈለገው ጊዜ ከመረጃ ክምችቱ መሃል መዞ የማውጣት ችሎታ ነው፡፡

7. መልዕክት ማስተላለፍ

ማብራሪያ፡ "የተገኘው መረጃ ወዲያውኑ ወይም በመጨረሻ በጥቅም ላይ የሚውልበት ዘዴ ሲሆን ይህም በጽሁፍ፣ በንግግር፣ በዳንኪራና በሌሎች ኪነጥበባዊ ዘዴዎች የሚገለጹበት፣ በተለይም ጽንሰ ሃሳቡ የሁሉም ተግባራት ቁንጮ የሆነውን ማለትም ማሰብን ያጠቃልላል፡፡ በገጽ 7 በሰፈረው መግቢያ ላይ የተዘረዘሩትን የንባብ ማስተዋል ችግሮች በዚህ ላይ በተጠቀሱት መረዳት እርከኖች አማካይነት ሊወገድ ይችላል፡፡ ሌሎች ተጽዕኖዎች ለምሳሌ እንደአካባቢ ቀን፣ ሰዓት፣ የሃይል ደረጃ፣ ተነሳሽነት፣ ጤና የፍላጎት ደረጃ በምዕራፍ ስድስት ተካተዋል፡፡

## <u>የማንበብ ችግርን ድል መንሳት</u>

### የማንበብ ችግር ለምን ሊኖር ቻለ?

ብዙዎቻችን ስለ ንባብ እና ስለማንበብ ችሎታችን የተሳሳተ ግምት አለን፡፡ እስቲ አንዴ ቆም ብለህ የንባብ ችግርህ ምን እንደሆነ አስብበት፡፡

ሊያጋጥሙን ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ራዕይ ፍጥነት ግንዛቤ ጊዜ መጠን ማስታወሻ ጠብቆ ማቆየት ፍርሃት ድካም ድብርት ትንተና ድርጅት ማፈግፈግ ማስታወስ የቃላት ክምችት የለሆሳስ ንባብ ምርጫ ገሸሽ ማድረግ ትኩረት በንባብ ወቅት ወደ ኋላ መመለስ**

በመጀመሪያ አይንህ እስከሚያርፍበት አድማስ ድረስ አሻግረህ እየተመለከትክ በአንዲት ነጥብ ላይ አተኩር፣ ከዛ በኋላ

- የግራ የቀኝ ሁለቱን ጠቋሚ ጣቶችህን በማነካካት አግዳሚ መስመር ለመፍጠር ሞክር እናም በአፍንጫህ ትይዩ 10 cm አርቀህ ለተወሰነ ጊዜ ቆይ ።
- እይታህን ሳትነቅል እና አግዳሚ መስመርህንም ሳትለቅ ጠቋሚ ጣቶችህን እያሽከረከርክ (እንደሚሾር እንዝርት ) ጣቶችህን በቀጥታ አራርቃቸው።

ከአድማስ ባሻገር ዕይታህን እና ትኩረትህ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቋሚ ጣቶችህን እያሽከረከርክ እና አግዳሚ መስመርህን ሳትለቅ ጠቋሚ ጣቶችህን አለያያቸው። (ይህን በምታደርግበት ጊዜ እጅህን እና ክርንህን መሰጠጥ ይኖርብሀል። ዱሩ ግን እንቅስቃሴህ ከአግድሞሽ መስመሩ ማፈንገጥ እንደሌለበት አትዘንጋ)

ጣቶችህ ከእይታ ውጪ እስኪሆኑ ድረስ እና የአግድሞሽ መስመሩን ሳይለቅ የመለጠጡን ሂደት ቀጥልበት።

- በግራና በቀኝ ጠቋሚ ጣቶችህ መካከል ያለውን ርቀት አስለካው። አሁንም እንደገና ልምምዱን እንቀጥል። ነገር ግን አንደኛውን ጠቋሚ ጣት በራስጌ ሌላኛውን ደግሞ በግርጌ በወራጅ መስመር አነካካቸው። አሁንም እንደገና በግምት በ10 cm ርቀት በአፍንጫህ ትይዩ ለተወሰነ ጊዜ አቆያቸው።

የአድማስ ባሻገር እይታህና ትኩረትህ በርቀት ነጥብ ላይ እንደተጠበቀ ሆኖ ወራጅ መስመርህን ሳትለቅ ጠቋሚ ጣቶችህን እያሽከረከርክ አንዱን ሽቅብ ሌላውን ቁልቁል በመሳብ ከእይታህ ክልል ውጪ እስኪሆኑ ድረስ ቀስ በቀስ በመሳብ አራርቃቸው።

ከዚህ በፊት እንዳደረከው ሁሉ በጠቋሚ ጣቶችህ መካከል ያለውን ርቀት አስለካ።



በሌላ ነጥብ ላይ በምታተኩርበት ጊዜ የቱን ያህል ለማየት እንደምትችል ማወቅህ ሳያስደንቅህ አይቀርም። ግን ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

ምስጢሩ ለየት ካለው የሰው ልጅ አይን አፈጣጠር የተነሳ ነው። የእያንዳንዱ ዐይናችን የዕይታ ድራብ (Retina) 130 ሚሊዮን ብርሀን ተቀባይ አካል አለው። ይህ ማለት ሁለቱ ዐይኖቻችን 260 ሚሊዮን ብርሀን ተቀባይ አካል አላቸው ማለት ነው።

ማዕከላዊ እይታችን (መፅሀፍ ስናነብ ወይም በርቀት ስንመለከት የምንጠቀምበት ክፍል) 20 % የሚሆነውን ብርሀን የመቀበል እና በጥቅም ላይ የማዋል ብቃት ያለው ሲሆን፣ ቀሪው 80% የብርሀን መቀበያ አቅም ለዳርቻ (ለጠርዝ) እይታ ብቻ የሚዉል ነው።

የጠርዝ (የዳርቻ) እይታህን በንባብ ወቅት እየተጠቀምክ በሄድክ ቁጥር ስፊና በጥቅም ላይ ያልዋለውን እምቅ የዳርቻ እይታህን (የአዕምሮ ዕይታህን) መጠቀሙን እየተላመድከው ትሄዳለህ ማለት ነው። የአዕምሮ ዕይታ ስል ምን ማለቴ ነው? በዐይንህ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ አዕምሮህን በመጠቀም ማንበብና ማየት ማለት ነው። ይህም ዮጋ፣ ፀሎትና የተመሥጦ ልምምድን በሚያዘወትሩ ሰዎች ዘንድ በሰፊው የታወቀ ፅንስ ሀሳብ ነው። እናም ማናቸውም ‹‹ማጂክ ዐይን›› ወይም የሶስት እዮሽ እይታ በሚማሩ ሰዎች ዘንድ የታወቀ ነው።

በአዕምሮ ዐይኖችህ ተመልከት

የሚቀጥለውን ልምምድ መመሪያ ካነበብክ በኋላ ወደ ገፅ 139 ሂድና ‹‹የማዕከላዊ ትኩረት›› ከምትለው ቃል ግርጌ ስር ጠቋሚ ጣትህን አሳርፍ።

- አይንህ እዛው ማዕከላዊ ቃል ላይ ትኩረቱን ሳይለቅ ዳርና ዳሩን ስንት ቃል ላይ እንደሚያርፍ አጢነው።
- ጣትህን ካሳረፍክበት ጎን እና ጎን ራስጌና ግርጌ ስንት ቃላት እንደሚታዩህ ልብ በል።
- በገፁ ግርጌና ራስጌ ቁጥሮች ተፅፈው እንደሆነና እነዛም ቁጥሮች ምን (ስንት) እንደሆኑ መናገር እንድትችል ተመልከት።
- በገፁ ላይ ምን ያህል አንቀፅ (ፓራግራፍ) እንዳለ ልብ በል።
- በተቃራኒው ገፅም ላይ ስንት አንቀፆች እንዳሉም ልብ በል።
- ከሁለት አንደኛው ቀኝ ገፅ ላይ የትኛው ላይ ነው ምስል ያለው?
- ምስል ካለስ ምንድን ነው ለማብራራት የሚሞክረው?

ብዙ ሰዎች ለነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡት መልስ "አዎን" የሚል ነው ? ይህም የሚጠቁመው አብዛኞቻችን የዳርቻና የማዕከላዊ ዕይታችንን በመጠቀም የማንበበ ተፈጥሮአዊ ብቃት አለን ማለት ነው። በዚህ ዘዴ 260 ሚሊዮን ብርሀን ተቀባዮቻችንን እየተጠቀምን ግንኙነታችንን እና አንጎላችንን እያበለፀግን እንሄዳለን ማለት ነው።

ከእንግዲህ ወዲህም ይህን ስርነቀል ዘዴ በመጠቀም በዐይንህ ብቻ ሳይሆን በአንጎልህም ታነባለህ ማለት ነው። በገፅ 139 ላይ የተቀመጠው ምስል በግልፅ የሚያሳየው ሁላችንም የምናዘወትረው ማዕከላዊ እይታ ሲሆን በዙሪያ ያለው ነብ ደግሞ የሚያሳየው፣ ፍላጎታችን ከሆነ፣ በጥቅም ልናውለው የምንችለውን የዳርቻ እይታ እንዳለን ያመለክታል።



**የዕይታ ዲላማ ወረዳ፡** የውስጠኛው ክብ መስመር የሚያሳየው ፊጣን አንባቢ አይንና /አንጎሉን ከተጠቀመ የሚያነበውን ነገር በቅርብ ርቀት ጥርት አድርጎ የሚያይበትን ወረዳ ሲያመለክት፣ የውጭው ክብ መስመር ደግሞ የዳርቻ ወይም የጠርዝ ክልል ዕይታን እንዳለ ያመለክታል።

<u>የንባብ አቅም</u>

- የዳርቻ ክልል ዕይታህን እና የማዕከላዊ ትኩረት ዕይታህን በአንድ ላይ ማቀናጀት ከቻልክ፣ በአንድ ገፅ ወይም አንቀፆች ላይ የሠፈረውን መረጃ በአንዴ ልትረዳው ትችላለህ።
- ከውትሮው በተለየ መልኩ መፅሀፍህን አርቀህ በመያዝ የዳርቻ ክልል ዕይታ ችሎታህን እያጎለበትክ ትሄዳለህ።ይህም የዳርቻ ክልል እይታህ በየጊዜው እየተሻሻለ እና እየጎለበተ ይሄዳል፡፡
- የማዕከላዊ እይታህ መስመር በመስመር እየሄደ ዝርዝር ሁኔታዎችን ሲያጠና የዳርቻ ዕይታ ደግሞ እየተነበበ ያለውን ሲከልስ ወይፊቻ የሚነበበውንም እየገመገመ ይሄዳል ።
- ይህም ልምምድ በዐይን ጡንቻዎች ላይ ጫና ከኮምፒዩተር ለዐይን በጣም ቀላል ይሆናል፡

Arada Sub City Wereda 10 ... Culture Arts & Tourism

ይጠቀማል። ሙዚቀኛ ለሆነ ሰው ይህ ለሃሣሣድ ቀለል ያለ ይሆንለታል፤ ምክንያቱም ይህ ዘዴ ሙዚቃን ከማንበቢያ ስልት ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ነው።



### ተለዋጭ የጠረጋ ንባብ

ተለዋጭ የጠረጋ ንባብ ዘዴ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው ዘዴ ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በአንድ ወሳኝ ነጥብ ላይ ግን ይለያያል። ይህ ዘዴ አቅምህ እስከፈቀደ ድረስ በአንድ ጊዜ በርከት ያሉ መስመሮችን ማንበብ ያስችላል።



### የተገላቢጦሽ የጠረጋ ንባብ

ይህ ዘዴ ከላይኛው ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በአንድ ወሳኝ ነጥብ ላይ ግን ይለያል።ይኸውም ይህ ዘዴ ሂደቱን በመቀየር በተገላቢጦሽ መስመር እያንዳንዱን የገፅ መስመር ይቃኛል። ይህም ዘዴ ግራ የሚያጋባ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ዐይናችን

በአንድ ትኩረት አምስት /ስድስት/ ቃላትን በአንድ ጊዜ የሚቃኝ መሆኑን ካልዘነጋን ነገሩ እምብዛም ግራ አያጋባንም፡፡

ወደኋላ በምታነብበት ጊዜ በአዕምሮህ ውስጥ ያለውን መረጃ ሁሉ በእያንዳንዱ መጀመሪያ መስመር ላይ ያለውን ትክክለኛ ምስጢር እስከሚከሰትልህ ድረስ ያለውን መረጃ እያከማቸህ ትሄዳለህ ማለት ነው፡፡ ይህም ቁርጥራጭ ምስሎችን የማገጣጠም ጨዋታ በምንጫወትበት ጊዜ ቀሪውን ምስል ከማግኘት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይህም ድርብ ጠቀሜታ ሲኖረው፤ በምታነብበት ጊዜ በተጓዳኝ እያስተካከልክ ትሄዳለህ ማለት ነው፡፡ ይኸም የማንበብ ፍጥነትህን እያጎለበተ የትኩረትህንና መዕሀፍትን የመረዳት ሀይልህን ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ያደርገዋል፡፡



እያንዳንዳቸው ከላይ የተጠቀሱት የጠረጋ ንባብ ዘዴዎች በግልብ አንኳር አንኳሩን በምንቃርምበት ጊዜ ወይም በፍጥነት መፅሀፍትን መልከት በምናደርግበት ጊዜ ወይም ዳግም ብዙ መስመሮችን ለማንበብ በምንፈልግበት ጊዜ የምንጠቀምበት ነው፡፡ የጠረጋ ንባብን ማሳጠርም ማስረዘም ትችላለህ፡፡ ይኸውም በአንድ ጊዜ የምታነበው መስመር በመቀነስ ወይም በመጨመር አሊያም ከአንድ በላይ ዘዴዎችን በማቀናጀት ልትጠቀምበት ትችላለህ፡፡

እየተለማመድክ በምትሄድበት ጊዜ የንባብ ፍጥነትህ እያደገ ነገሮችን የመረዳት አቅምህም በፍጥነት እየጨመረ ይሄዳል፡፡

ለማንበብና ለማወቅ በተመቻቸ ሁኔታ ላይ ትገኛለህ፤ ስለዚህ አካባቢህን በተቻለ መጠን የሚያነቃቃና የሚያበረታታ ማድረጉ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

**አቀማመጥና የመብራት መጠን**

በተቻለ መጠን ንባብና ጥናትህ በቀን ብርሃን ቢሆን ይመረጣል። ስለዚህ የማንበቢያ ወይም የመፃፊያ ጠረጴዛ ከመስኮቱ ባይርቅ ጥሩ ነው። በሌላ ጊዜ፤ ሰው ሰራሽ የመብራት ፋና ግራ ትከሻህን አልፎ (በቀኝ እጅህ የምትጠቀም ከሆነ) መምጣት ይኖርበታል። መብራቱ የሚነበበውን ጽሁፍ ደመቅ አድርጎ የሚያሳይ መሆን አለበት፤ ይህም ሲባል እቤቱ ውስጥ ካለው መብራት ጋር በሚጻረር መልኩ እምብዛም ደማቅ መሆን የለበትም።

**የመማሪያ መጽሐፍ በአካባቢው መኖር**

እንጎልህ በምቾትና በትኩረት እንዲሰራ ከፈለክህ፤ ለስራህ የሚያስፈልጉህ የትምህርት መሳሪያዎች በእጅህ ልትደርስበት በምትችለው ርቀት መቀመጣቸው ጠቃሚ ነው። ይህም ዝግጁና የተዝናናህ ስሜት ስለሚኖርህ በሥራህ ላይ የበለጠ ለማተኮር የተመቻቸ ሁኔታ ላይ ትገኛለህ።

**አካላዊ ምቾት**

ራስህን በጣም የተመቸህ ማድረጉ ደግሞ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፤ ምክንያቱም ምቾቱ አትኩረህ ከመስራት ይልቅ እንቅልፍ እንቅልፍ እንዲልህ ሊያደርግህ ይችላል። በተቻለ መጠን ወንበርህ ቀጥ ያለና የጀርባ ድጋፍ ያለው ሆኖ እምብዛም ደረቅ ወይም ምቾት የበዛበት መሆን የለበትም። በምቹ ሁኔታ የሚያስቀምጥህና አቀማመጥህን ጥሩ የሚያደርግ መሆን አለበት።

**የወንበርህና የጠረጴዛህ ከፍታ**

ወንበርህ ከፍ ያለና ጭንህን ከወለሉ ጋር ትይዩ የሚያደርግ መሆን አለበት። ይህም የመቀመጫ አጥንትህ ጫናውን በትክክል እንዲሸከም ያደርገዋል። ከመቀመጫ ወንበርህ በአማካይ በ20 ሳንቲሜትር ከፍያለ መሆን አለበት።

እነዚህንም ቅድመ ቅጥያዎች ከቃላት በፊት እያስቀመጥክ በአግባቡ ከተጠቀምክባቸው እምቅ የቃላት ችሎታህን ቢያንስ በ10,000 አሳደክው ማለት ነው፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ በምታነብበት ወቅት እነዚህን ቅድመ ቅጥያዎች ልብ በላቸው፡፡

**ቁልፍና ቅድመ ቅጥያዎችን የያዙ ቀዳሚ ቃላት**

| ቃላት | ቅድመ ቅጥል | መደበኛ ትርጉም | የቃሉ መሰረት | መደበኛ ትርጉም |
|---|---|---|---|---|
| Precept | Pre- | በፊት | Capere | ወሰደ፣ጨበጠ |
| Detain | De- | ርቆ፣ተለይቶ/ወደታች | Tenere | ያዘ፣አለ |
| Intermittent | Inter- | መካከል | Mittere | ላከ ? |
| Offer | Ob- | ከ----- አንፃር<br>በ----- ላይ | Ferre | አስገኘ፣ተሸከመ |
| Insist | In- | ወደውስጥ | Stare | ድርቅ አለ፣ተጋተረ |
| Monograph | Mono- | ለብቻ፣አንድ | Graphein | ጻፈ |
| epilogue | Epi- | ወደ | Specere | አየ |
| Advance | Ad- | በ--- ላይ | Logos | ንግግር |
| Uncomplicated | Un- | መራራቅ<br>በአንድነትአለመሆን | plicare | አጠፈ |
| Non-extended | Non- | ውጪ፣ባሻገር | Tendere | ዘረጋ |
| Re-production | Re- | እንደገና፣ወደኋላ | Ducere | መራ |
| indisposed | In- | የአፍራሽምልክት | ponere | አስቀመጠ፣አኖረ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | Dis- | ለየየ | | |
| Over sufficient | Above- | ከልክበላይ | Facere | ስራ፣አደረገ |
| | Sub- | ቢታች | | |
| Mistranscribe | Mis- | በተሳሳተ-- | scribere | ጻፈ |
| | trans- | ባሻገር--- ማዶ | | |

## የድህረ ቅጥሎች (Suffixes) ጥንካሬ

ድህረ ቅጥሎች ማለት ከሌሎች ቃላት ኋላ እየተቀጠሉ የቃላትን ትርጉም የሚቀይሩ ናቸው። ብዙዎቹ ድህረ ቅጥሎች የአንድ ነገርን መለያ ባህርይ ወይም ዓይነትነትን ወይም ደግሞ አንድ የንግግር ክፍል ወደ ሌላ ሲቀየር (ለምሳሌ ከቅፅል ወደ ግስ) የሚገልፁ ናቸው።

# ስለሩ አራቱ ድህረ ቅጥሎች

| ድህረ ቅጥል | ትርጉም | ምሳሌ |
|---|---|---|
| - Able.ible (L) | የሚችል | መቆየት የሚችል፣ዕድሜ ያለው |
| - Al.ail(L) | ከ------ጋርየተያያዘ | ከሆድ፣ከከርስ |
| - Ance,ence,<br>- ant(L) | - ቅርፅ የመያዝ ድርጊት<br>- የባህሪ ቅዕልን የሚያሳይ የግል ወኪል፣ውጤት የሚያስከትል ድርጊት | ኢንሹራንስ፣ወፍራም ጡንቻ<br><br>የሚጋተር፣የሚያገለግል |
| - Ation,-ition(L) | የነገር ስም | ሁኔታ |
| - er | ወገንተኝነትን የሚያሳይ | ውድቀት፣ፍርስርስ‐ወጣ |
| - er | ወገንተኝነትን የሚያሳይ | ገበሬ፣ኒውዮርካዊ |
| - ism | አስተምሮን የሚገልፅ | ሶሻሊዝም፣ሪያሊዝም |
| - ive(L) | ባህሪይ፣ፀባይ | ፈጣሪነት፣ተቀባይነት |
| - ize,-ise(L) | አድራጊነትን የሚገልፅ | አዲስ ማድረግ |
| - Logy (G) | የእውቀት መስክን የሚገልፅ(ስነ) | ባዮሎጂ፣ስነ‐ፍጥረት፣ስነ‐ልቦና |
| - Ly(E) | የ— ባህሪያለው | በፍጥነት፣በዝግታ፣በቀስታ (በነገር ስም ላይ እየተለጠፈ<br><br>ሁኔታን የሚገልፅ) |
| - Or(L) | አድራጊነትን የሚገልፅ | አሸናፊ፣ሃይል አመንጪ |
| - Ous,-ose | የተሞላ | በጎደይነት የተሞላ፣ በስጋት የተሞላ ሽቁጥቁጥነት፣<br><br>ድብርተኝነት |
| - some | መሰል | ደስተኛ መሰል |
| - Y(E) | ሁኔታ(ነት--) | አስቸጋሪነት |

***ፍቺ፣ G (ግሪክ) L(ላቲን) F(ፈረንሳይ) E(እንግሊዝ)

# አስራ አራቱ መሰረታዊ ቃላት

| መሰረታዊቃል | ትርጉም | ምሳሌ |
|---|---|---|
| Aer | አየር | አየር የበዛበት፣አውሮፕላን |
| Am(amare) | ፍቅር | ተፈቃሪነት፣በውዴታ አንድ የሆነ ስራ ለመስራት የገባ፣ተወዳጅ |
| Chron | ጊዜ | ጊዜን በትክክል መቁጠር /ማስቀመጥ/ የቆየ፣ስር የሰደደ |
| Dic,dict | አለ፣ተናገረ | ተናገረ |
| Equi | እኩሌታን የሚጠቀም | እኩልርቀት |
| Graph | ፃፈ | ቃም ፅሁፍ፣አፃፃፍን የሚያጠና |
| Luc(from lux) | ብርሃን | ማብራራት |
| Pot, poss, poten | ቻለ | ችሎታ፣የሚችል |
| Quarere | ጠየቀ፣ፈለገ | ጥያቄ፣ምርመራ፣መጠይቅ |
| Sent, sens (from sentire) | መስማት | የሚሰማው፣ስሜታዊነት |
| Soph | ጥበብን የሚወድ | ጥበብን የሚወድ |
| Spect (form spicere) | ተመለከተ/አየ | ወደ ውስጥ የሚመለከት፣ውስጥን መፈተሽ |
| Spir(from spirare) | ተነፈሰ | አነሳሽ ኃይል |
| Vid,vis(videre) | ተመለከተ | የበላይ ተመልካች፣ዕይታ፣ወደፊት የሚያይ |

ይህ አበረታች ዜና ሊታይ የሚገባው የንግዱ ማህበረሰብ አንገብጋቢ ነው ብሎ ባመነበት ችግር ዙሪያ ነው።

ባለፉት 20 ዓመታት በመላው ዓለም የሚኖሩ ከ100,000 ሰዎች በላይ የሚሆኑ ሀሳብ እንዲሰጡ ተጠይቀው ነበር። እነዚህም ሰዎች መሻሻል ይኖርባቸዋል ብለው ካመኑባቸው 20 ከፍተኛ ጉዳዮች የጠቀሷቸው የሚከተሉት ናቸው።

1- የንባብ ፍጥነት
2- እንብቦ መረዳት
3- አጠቃላይ የጥናት መርሐግብር
4- የመረጃ ጎርፍን ስርዐት ማስያዝ
5- የማስታወስ ሀይል
6- አትኩሮት
7- የንግግር ብቃት
8- የአፃፃፍ ብቃት
9- አዲስ ሀሳብ ማፍለቅ
10- ዕቅድ
11- ማስታወሻ አያያዝ
12- ተግዳሮትን መተንተን
13- መፍትሔ መሻት /መፈለግ/
14- የሚያነሳሳ ዓላማ
15- ትንተናዊ አስተሳሰብ
16- የፈተና ዘዴ
17- ቅድሚያ መስጠት
18- ጊዜን በአግባቡ መጠቀም
19- መረጃን ጥቅም ላይ ማዋል
20- ዛሬ ነገ ማለት (መጀመር)
21- ከዕድሜ ጋር ተያይዞ የሚመጣ የአእምሮ ድክመት

በዘመናዊ ጥናትና ምርምር በመታገዝ ስለአንጎል አሠራር በተደረገው ጥናት እነኚህ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ቀለል ባለ መልኩ ሊፈቱ እንደሚችሉ ታምኖበት ምርምር እየተካሄደ ነው። ይህም ምርምር የሚከተሉትን ይዳስሳል።

- የአንጎል ግራና ቀኝ ክፍሎች አሰራር

(ሀ) እውነት

(ለ) ሃሰት

2. በየዘርፉ የተመደቡ የብሔራዊ ኦሎምፒክ ቡድኖች ስፖርቱ ከመደቡት የዘውትር ክፍለ ጊዜ የሚቀጥለውን መቶኛ (%) የአእምሮ ግንባታ፣ አይበገሬነትና ስለልቶ አይታ ሥልጠና ያውሉታል፡፡

(ሀ) 20 %

(ለ) 30 %

(መ) 40 %

(ረ) 50 %

3. "የአዕምሮ ንቃት" ሚኒስተር ተብሎ የተሾመው ሰው ማን ይባላል?

(ሀ) ዶ/ር ማርዮን ዳይ

(ለ) ዶ/ር ሉዊስ አልቤርቶ ማቻዶ

(መ) ዶሚኒክ አብራይን

(ረ) ፐላቶን

4. ስሌት በአብዛኛው የግራ አንጎላችን ተግባር ነው፡፡

(ሀ) እውነት

(ለ) ሃሰት

5. የዓለማችን አይንስታይኖች፣ ኒውተኖች፣ ሴዛኖችና ሞዛርቶች ስኬታማ ሊሆኑ የበቁት ቀጥሎ የተመለከቱትን በማቀናጀት ነበር፤

(ሀ) ቁጥርን ከሎጂክ

(ለ) ቃላትን ከትንተና

(መ) ህብረቀለምን ከትንተና

(ረ) ትንተናን ከአይነ ህሊና (ኢማጂኔሽን)

6. በአእምሮ ካርታ ሥራ በመሃል የምታኖረው

(ሀ) ምስልን

(ለ) ቃልን

(መ) ምንም አታኖርም

(ረ) ያለማስለስ ቃልና ምስል

7. እጅግ ፈጣንና የተግግዘ ንባብ ዘዴን በመጠቀም ከሚቀጥሉት ቃላት በደቂቃ (ቃ.ደ) በላይ ፍጥነት ሊኖርህ ይችላል፣

(ሀ) 500 ቃ.ደ

(ለ) 1000 ቃ.ደ

(መ) 10000 ቃ.ደ

(ረ) 100000 ቃ.ደ

8. መጽሐፍትን ለማጥናት የአእምሮ ፈጥኖ ደራሽ ሃይል የፈጠሩት ድንበር ዘለል ኩባንያዎች የሚቀጥሉት ነበሩ፡-

(ሀ) አይቢኤምና ኮካኮላ

(ለ) ዲጂታልና ናቢስኮ

(መ) ናቢስኮና ማይክሮ ሶፍት

(ረ) አይቢኤምና አይሲኤል

9. የማንጠልጠል ዘዴን (ኒማኒክስን) የፈለሰፉት ከሚከተሉት መካከል አንዱ ነበር።

(ሀ) ቻይኖች

(ለ) ሮማውያን

(መ) ግሪኮች

(ረ) ፕላቶ

10. አንድ ሰዓት ካለፈ በኋላ

(ሀ) የማስታወስ አቅም መጠነኛ ከፍታ ያሳያል።

(ለ) የማስታወስ አቅም ይንደረበባል።

(መ) የማስታወስ አቅም ለአጭር ጊዜ ዝቅ ይላል።

(ረ) የማስታወስ አቅም ባፋጣኝ ይቀንሳል።

11. አንድ የመማር ክፍለ ጊዜ ካለፈ ከ24 ሰዓት በኋላ ቀጥሎ በተመለከተው መቶኛ (%) የተማሩት ይረሳል፤

(ሀ) 60 %

(ለ) 70 %

(መ) 80 %

(ረ) 90 %

12. መደበኛው የአንጎል ህዋሳት ቁጥር ቀጥሎ በተመለከቱት አሃዞች በአንዱ ይሰላል፡-

(ሀ) አንድ ሚልዮን

(ለ) አንድ ቢልዮን

(መ) አንድ ትሪሊዮን

(ረ) አንድ ትሪሊዮን ጊዜ ትሪለዮን

13. የክሬይ (Cray) ኮምፒውተር አጠቃላይ የሥሌት አቅሙ ከሰው ልጅ አንጎል የሥሌት ሃይል ጋር እየተስተካከለ ነው

(ሀ) እውነት

(ለ) ሃሰት

14. ከዶ/ር ማሪዮን ዳይመንድ ጥናት በመነሳት በቅርቡ በተረጋገጠው መረጃ መሰረት ከሚቀጥሉት አንዱ የተረጋገጠ ሃቅ ሆኗል።

(ሀ) ንቁና ጤነኛ አንጎል ባለቤት የሆነ አዛውንት በእርጅናው ምክንያት የአንጎል ህዋሳቱ እየሞቱበት ይሄዳሉ ለሚለው ማረጋገጫ አልተገኘም።

(ለ) በማናቸውም ሰው አንጎል በእርጅና ምክንያት የአንጎል ህዋሳት እየሞቱ አይሄዱም።

(መ) ከ40 ዓመት በታች ባሉ ሰዎች ከእርጅና ጋር የተያያዘ የአንጎል ህዋሳት እየቀነሰ መሄድ ማረጋገጫ አልተገኘም።

(ረ) ንቁና ጤነኛ አንጎል ባለቤት በሆኑ አዛውንት እንኳ መጠነኛ የአንጎል ህዋሳት መቀነስ መድረሱን የሚያረጋግጥ መረጃ ተገኝቷል።

15. በሚቀጥሉት እድሜ ክልሎች እስከ አንዱ ድረስ ለደረሱ አዛውንት እንኳ የተሟላ የትምህርት መርሃ ግብር ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎች ከተመቻቹ፣ ቢያንስ ከስታቲስቲክ አንፃር ትርጉም ያለውና ዘላቂ የሆነ የአእምሮ መሻሻል ሊመዘገብ እንደሚችል ተረጋግጧል።

(ሀ) እስከ 60 ዓመት እድሜ

(ለ) እስከ 70 ዓመት እድሜ

(መ)እስከ 80 ዓመት እድሜ

(ረ)እስከ 90 ዓመት እድሜ

በእርግጥ፣ የእድገት አካሄድ ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም። የማንበብ ቅልጥፍና እድገትን ከተመለከትን ግን እድገቱን የሚወስነው አንጎላችን በራሱ ፍጥነት ጽሑፎችን የማብላላት አቅሙ ነው። እንደ ማናቸውም የክህሎት ስልጠና፣ ልምምድን ይጠይቃል፤ ሲጀመርም እጅግ ግራ ሊያጋባ ይችላል። ሁቱ ግን፤ ክህሎቱን ከተካንከው በኋላ ቃላትንና አረፍተነገራትን እንደወትሮው ማንበብህን ፈጽሞ ታቆማለህ።

በመጀመሪያ ሙከራዎችህ "ፎቶ ሪዲንግ" አስቸጋሪ እንደሚሆንብህ የታወቀ ነው። ሀሳቡ ራሱ እንግዳ መሆኑንና ዐይን ሳያይ አነበለሁ ማለት የማይቻል ነገር መሆኑ ይታይሃል። በርግጥ ግራ መጋባትና ጥቂት መደናበርም እንደሚኖር የታወቀ ነው። ይህም በብዙዎች ላይ የሚከሰት እና ያለ ነገር ነው። ልትዘነጋው የማይገባ ነገር ቢኖር ሳይንሳዊ ሕግ ውሉን የማይስት መሆኑ ነው። ጥቂት ታገስ፣ በጥረትህ ትደሰታለህ።

ሥራችንን ከመጀመራችን በፊት አንድ ማሳሰቢያ መስጠት ተገቢ ይሆናል። የፎቶ ሪዲንግ ቴክኒክ በጽሑፍ መልክ ሲገለጥ ረጅም ሐተታን የሚጠይቅ ነገር ነው። ነገሩን ለማሳጠር ሲባል በግዴለሽነት አንዳንድ ቁም ነገሮችን ብንዘል ለሕሊናችን ታማኝ አይደለንም ማለት ነው። ስለዚህ በኛ በኩል የምንለግስህ ምክር የሥልጠናው ጠቅላላ እውቀት እስኪገባህ ድረስ ቴክኒኩን ደጋግመህ እንድታነበው ነው። ልታደርገው ያቀድከውን ጉዳይ ጠቅላላ ቁመናውን በትክክል ከተገነዘብከው፤ ቴክኒኩን ከልብ ለመተግበር በራስህ ላይ ሙሉ እምነት ያድርብሃል።

## የፎቶ ሪዲንግ ቅድመ ዝግጅት

### እርከን 1

ልታነበው የምትሻውን ጽሑፍ ከፊትህ ዘርጋው ዓይንህን ጨፍንና ተዝናና፤ እተነፋፈስህ እስከታች የሚዘልቅና የትንፋሽህ ወጣ ገባ እንዳይዛነፍ ይሁን።

ካንተው ከራስህ በስተጀርባ አንተው ራስህ በመንሳፈፍ ላይ ነህ እንበል፤ ተንሳፈህ እያለ ከጭንቅላትህ በላይ ሆነህ እንደምታነበው ምስል። ይህ የመንሳፈፍ ቴክኒክ ሁለቱን ተነጻጻሪ ገጾች በአንድ ለማየት እንድትችል አበቃህ ማለት ነው።

ይህን መጽሐፍ እንድታነብ ምክንያት የሆነህን ነገር ግለፅ፤ ምን ጥቅም ታገኝበታለህ ? በጽሁፉ ላይ ካሉት ዝርዝር ሁኔታዎች ስንቶቹን ነው ልታስታውስ የምትፈልገው? መጽሐፉን ለማንበብ ምን ያህል ጊዜ ነው የመደብከው?

ቀጥሎም የመጽሐፉን ጠቅላላ ቁመና ለመገምገም ትበቃ ዘንድ፤ ይዘቱን ርእሶቹን የየምዕራፎቹን ንዑስ ርእስ እና በሽፋኑ ፊትና ኋላ ገጾች ላይ የተጻፉትን ቃኝ፤ቅኝቱን በምታካሂድበት ወቅት ቁልፍ የሆኑ አንዳንድ ቃላት ተድበሰብሰው እንዳይቀሩ ልዩ ጥንቃቄ አድርግ።

ቅኝቱን ካበቃህ በኋላ በእርግጥ መጽሐፉን ለማንበብ ያስፈልግ እንደሆነ ወስን። መልሱ አዎ ከሆነ ወደሚቀጥለው እርከን ሂድ። አብዛኛውን ጊዜ የሚያስፈልግህን መረጃ ሁሉ ከምታደርገው የተሟላ ቅኝት የምታገኘው ይሆናል። በዚህ ዓይነት ጊዜና ጉልበት ትቆጥባለህ።

## ፎቶ ንባብ

### እርከን 2

እንደገና ዓይንህን ጨፍንና እስከ መጨረሻው ወደ ውስጥና ወደ ውጭ ተንፍስ፤ ወደ ውጭ በተነፈስክ ቁጥር "ተዝናና" የሚለውን ቃል እያሰላሰልክ ሙሉ ሰውነትህን ጥቂት ጊዜ ወስደህ አሳርፈው፤ ይህን በምታደርግበት ጊዜ ዋና ዋና የሚባሉ የሰውነት አካላትህን ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጣት አፍታታቸው። አጠር ያለ የቪዥዋልይዜሽን (የአእምሮ እይታ) ልምምድ ይህን ሁሉ ሊያከናውንልህ ይችላል፡

እስተዋጽኦ ምንድነው? እነዚህ ጥያቄዎች ስለመጽሐፉ የሚኖርህን የማወቅ ፍላጎት ለመቀስቀስ የሚረዱ ከመሆናቸው አልፎ ስውር አእምሮህ ሥራ እንዲጀምር የሚያነቃቁት ናቸው::

በተጨማሪም፣ እነዚህ ጥያቄዎች ባነበብከው መጽሐፍ ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ጥቅሶችን አዲስ ምልክታ ታደርግባቸው ዘንድ ጉጉትህን ይቀሰቅሳሉ:: ጉጉትህን ለማርካት ይበጃል የምትለውን አንዱን ጥቅስ እንደገና ተመልከተው:: ያነበብከውን እያንዳንዱን መጽሐፍ ከመሃሉ ጀምረህ እየቃኘህ ስትዘልቅ ጥቂት ቆም ልትል የምትችለው ለአእምሮህ እንግዳ የሆነ ቃል ወይም አባባል ያጋጠመህ ከሆነ ብቻ ነው:: በቂ መረጃ እስከታገኝ ድረስ እያንዳንዱን ጥቅስ አንድ ሁለት መስመር አንብብ:: ሌሎችንም ጥቅሶችንም በዚሁ አይነት ልትቃኛቸው ትችላለህ:: በአጠቃላይ ደመ ነፍስህን ተከትለህ ስትዘልቅ ስውር አእምሮህ ወደ ምትሻው መረጃ ይመራህ ዘንድ ሁኔታዎችን አመቻች:

አላስብንበትም እንጂ፤ የምናነባቸው ብዙዎች ቃላት ደራሲው በድልዳልነት ብቻ እንዲያገለግሉ አረፍተነገሩን ያቀናጃሉ ሲል የተጠቀመባቸው አላስፈላጊ ቃላት ናቸው:: ከዚህ ውስጥ ይጠቅሙኛል ብለህ የምትቃርማቸው በጣም አስፈላጊ ቃላት ጥቂት ሲሆኑ ሌሎቹን ብዙም አላስፈላጊ እና ትርጉም የለሾችን ገሸሽ ልታደርጋቸው ትችላለህ::

## ነፃ ማስታወሻ፡ ሀሳብን በተከሰተበት ጊዜ መፃፍ

ቀደም ሲል ባቀረብነው ምዕራፍ ታላላቅ ፈላስፋዎች ጠቃሚ እይታዎችን እንደሚመዘግቡ ማስታወሻም እንደሚይዙ አውርተን ነበር:: ማስታወሻዎቹ ያንድን ጂኒየስ አእምሮ አሰራር ዘዴ እንገነዘበው ዘንድ እውቀት ፈንጥቀውልናል:: እነዚያው ታላቅ ፈላስፋዎች በእጅ ጽሑፋቸው ወይም በሌሎች ሰዎች መጻሕፍ ዳርዳር የጻፉአቸው ማስታወሻዎች ወይም ትችት ያንኑ ሐቅ ያረጋግጣሉ:: ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ላይ ማስታወሻ ማስፈር አጉል ፈሊጥ አድርገው ስለሚያዩት ይህን እንዳናደርግ ይመክሩናል:: የኋላ ኋላ ግን በመጽሐፍ ላይ ማስታወሻ መጻፍ የምሁርነት እውነተኛ መለያ መሆኑን ልንገነዘብ ቢቃን::

በእርግጥ ንብረትህ ባልሆነ መፅሐፍ ላይ ማስታወሻ መፃፍ በፍጹም የሚመከር አይደለም:: ከቤተ መፅሐፍ በምትዋሰው መጽሐፍ ላይ ማስታወሻ ተለትልቆበት ስታይ፣

## የጨለምተኝነት ዝንባሌ

የምታቀርበውን ሀሳብ ሁሉ ከጨለምተኝነት አንፃር ተመልከተው፡፡ የቱ ላይ ነው ሀሳቡ የተሳሳተ ነው የተባለው? ለምንድን ነው ምናልባት ችግሩ አይፈታም የተባለበት? ወዘተ ለእያንዳንዱ ጨለምተኝነት ዝንባሌ መፍትሄ ለማግኘት ሞክር፡፡

## የማመሳሰል መርህ

ያሰብከው ስራ ከሌሎች የባህል መስኮች ጋር እንዴት ሊያያዝ ይችላል ? ባንተ ሀሳብና በሳይንስ፣ ፖሊቲካ፣ ሥነጥበብ፣ ሕክምና፣፣ ውትድርና፣ ትምህርት ፍልስፍና ወዘተ ውስጥ ያሉ ተመሳሳይ ሃሳቦችን አነፃፅራቸው፡፡ ያሰብከውን ስራ ወይም ተግዳሮት ሊደግፉ ወይም ሊፈቱ የሚችሉ ነገሮችን በዚህ መስኮች ውስጥ ታገኛለህ?

## አጋናኝ

ያሰብከውን ስራ ወይም ተግዳሮትህ ከልክ ባለፈ አጋንነው፣ ውስንነቱንና የማድረግ አድሉን ለማወቅ አሁን ካለበት ሁኔታ የበለጠና የተሻለ ለማድረግ አሳድገው ወይም አሻሽለው፡፡

## አቃሳይ

አብሮ ለመስራት በማያስችል መልኩ ሀሳብህ ከልክ ያለፈ ገዘፎ ይሆን ? ለአስተዳደር አመቺ በሚሆን መልኩ ምናልባት አነስ ብሎ የሚቀርብበት ዘዴ ቢኖርስ ? አንድ ሀሳብ ሆነው እንዲቀርቡ ታስቦ አብረው የተለወሱ ብዙ ሀሳቦች ናቸው? አንዳንድ ጊዜ ካንድ ሀሳብ ጋር ከመስራት ይልቅ ከብዙ ትናንሽ ሀሳቦች ጋር መስራቱ ይመረጣል፡፡

## አሻሻይ

ሀሳብህ ወደፊትም ወደኋላም እልፍ የማይል ከሆነ ቅርጹንና ማንነቱን ለውጠው፤ አዲስ ቀለም ድምጽ፣ ቃና፣ ተግባር፣ ሽታ ወይም ስፋት ስጠው፡፡

## ሰፊ ተቀባይነት

ሀሳብህ ሰፊ ተቀባይነት ይኖረዋል ? በውስጡ በበለጠ ምቹ ማራኪ ወይም የተሟላ የሚያደርገው ነገር አለ ? ከሌለ ምናልባት እንደገና ቢገመገም አይከፋም፡፡

- ከወር በኋላ ---------------------የ2 ደቂቃክለሳ
- ከስድስት ወር በኋላ ---------የ2 ደቂቃ ክለሳ
- ከአመት በኋላ--------------------የ2 ደቂቃ ክለሳ

በዚህ አይነት መረጃው በረጅም ጊዜ የማስታወስ ኃይልህ ቋት ገብቶ ይከማቻል ማለት ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ክላስ የመጀመሪያ የአእምሮ ካርታህን ከመመልከት ይልቅ ለምታስታውሳቸው መረጃዎች ሌላ የአስቸኳይ ጉዳይ የአእምሮ ካርታ መስራት ተመራጭ ይሆናል፡፡ ምንም ሳትረዳ ምን ያህል ማስታወስ እንደምትችል ይህ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንንም ከመጀመሪያው የአእምሮ ካርታህ ጋር ታመሳክረውና ክፍተቶችን ለማስተካከል የማስታወስ ድክመት የሚታይባቸውን ቦታዎች ለማጠናከር ይረዳሃል፡፡

አሁን እየተሸጋገርንበት ያለነው ሃያ አንደኛው ምእተ ዓመት "የአእምሮ ካፒታል" ዘመን ነው። በአሁኑ ወቅት ከፍተኛውና ወሳኙ ክህሎት ***"መማርን እንዴት እንደምትማረው መማር"*** የሚለው ነው።

አሁን የተያያዝነው የሰው ልጅ እድገት ምዕራፍ ጠቃሚ መረጃን አውቆ በፍጥነት ማጣጣምና ይህንኑ ከነባር የመረጃ ቋት ጋር ማያያዝ፤ ከዚያም በተፈለገበት ወቅት በፍጥነት ወጪ ሊሆን በሚችል መልኩ በከምችት እንዲቆይ ማድረግ፤ በመጨረሻም እነዚህን ሂደቶች ሁሉ አልፈህ፤ ከተማርከው በመነሳት አንድ ነገር ፈጥረህ ያንን ተደራሽ ማድረግ መቻል የወደፊቱን ስኬት የሚወስን ሁኔታ ነው። አሁን፤ መጪውን ተግዳሮት ለመጋፈጥ ተገቢውን ትጥቅ ስንቀህል። መልካም እድል....

## የመሻሻል ስንጠረዥ

| የንባብ ቁጥር | ጊዜ (ደቂቃ-ሰከንድ) | ፍጥነት (ቃላት በደቂቃ) | የመረዳት ችሎታ |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |
| 6 | | | |
| 7 | | | |
| 8 | | | |
| 9 | | | |
| 10 | | | |

# የመሻሻል ግራፍ

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3000 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2000 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1500 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1250 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1000 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 900 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 800 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 700 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 600 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 500 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 400 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 300 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 200 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 100 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 0 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | የመሻሻል ሂደት |

"ይህ መጽሐፍ በቀላሉ አብራርቶ ደረጃ በደረጃ በግልፅ እንዳስቀመጠው የእውቀት ብርሀን የሰፈነበትን ዓለም በር ከፍቶ እንደመግባት ይቆጠራል።"

ሃይንዝ ኖርደን

(የኢንሳይክሎፒዲያ ኦፍ ኖውሊጅ የቀድሞ ዋና አዘጋጅ)

"አእምሮህ መጠነ ሰፊና ውስብስብ ሃሳቦችን ለማብላላት የሚችል ከመጠን በላይ ሃያል የሆነ ኮምፒውተር በመሆኑ ይህንን ሃይል ልትገራው ከቻልክ ምርምርና ጥናት ፈታኝና አድካሚ ስራ መሆኑ ቀርቶ ፈጣን ቀላልና ፍሬያማም ይሆናል።"

ቶኒ ቢውዛን (የማይንድ ማፕ ፈልሳፊ)

ለአስተያየትዎ

addis.mitket@yahoo.com

ኅትመት፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር
0111665352

ዋጋ ብር 130.00